# የሙላተ መለኮት ማብራሪያ

ቺካጎ፣ ኢሊኖይ፣ አሜሪካ

ኤፕሪል 25 1961B

1 አመሰግናለሁ ወንድም ካርልሰን። በጌታ ላላችሁ ወንድሞችና እኅቶች በሙሉሰላምታዬን አቀርባለሁ። አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ አይነት ድንቅ ምስክርነቶችን እና ሌሎች መሰል ነገሮችን ሳዳምጥ ከመቀመጫዬ ለመነሳት ትንሽ አቅማማለሁ። ዛሬ ጠዋት የገጠመኝ ተመሳሳይ ነገር ነዉ። በመከራና በስደት ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን፣ ባፕቲስት ወንድማችን እና እህታችን እንዳሳለፉት—ቀደም ሲል እኔ ራሴ ባፕቲስት ነበርኩ፣ ሚሲዮናዊ ባፕቲስት ሆኜ አገልግዬአለሁ። እናም የገዛ ወገኖቻችን ያደርሱብን የነበረዉን አዉቀዋለሁ....እኔም ተመሳሳይ ሁኔታ ዉስጥ ነበርኩ። የገዛ ወገኖቼ ተነሱብኝ፣ አብዷል ብለዉ ወደ ዉጭ ሊጥሉኝ ፈለጉ። እናም ገባኝ። ብዙዉን ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲህ እላለሁ፣ ካበድኩ፣ በቃ ብቻዬን ልሁን፣ ምክንያቱም በዚህ መንገድ ከትክክለኛ አእምሮዬ ይልቅ ደስተኛ ነኝ። ይህቺ ስለ ራሴ ያለችኝ ትንሽ ፍልስፍናዬ ናት።

2 በዚህ ጊዜ እና ሁኔታ በእርግጠኛነት እየተደሰትኩ ነዉ። እዚህ ያለው ከትንሿ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የመጣዉ ወንድም (ብዙውን ጊዜ እንደምንጠቅሰዉ) ወይም ካምቤል .... በመጀመሪያ አካባቢ ስብሰባዎችን ስናደርግ ከባድተቃዋሚ እንደነበሩ አስታውሳለሁ። ነገር ግን ታውቃላችሁ፣ ጳውሎስ የሚባል ልክ እንደኛ በተመሳሳይ ሁኔታ ዉስጥ የነበረ ሰዉ ነበረ፣ እናም እሱ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ.... ብዙውን ጊዜ የሚፈልጉት እናንተ የምትኖሩትን ሕይወት ይመስለኛል። ታውቃለህ፣ እኔ ከምሰብክ በማንኛውም ጊዜ ሕይወቴ ቢሰብክ ይሻላል።

3 ከተወሰነ ጊዜ በፊት ታላቅ አገልጋይ፣ ጥሩ የሙሉ ወንጌል ሰው.... ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ብዬ እገምታለሁ። ሬቨረንድ ቡዝ-ክሊቦርን ነበር—በሰባት የተለያዩ ቋንቋዎች ወንጌልን ይሰብካል። ችሎታ አለዉ.... የላቀ አዕምሮ ያለዉ ሰው ነው። በአንድ ወቅት እርሱ፣ ወንድም ሙር እና እኔ ሆነን አብረን እየተጓዝን የሆነ ነገር እየተነጋገርን ነበር። እኔ በእርሱ ሃሳብ ተቃርኖ ነበረኝ፣ ዞርያዬን ተመለከተኝ። እናም “መጽሐፍ ቅዱስህን አታውቀውም” አለኝ። (ወንድም ቡዝ እንዴት እንደሚናገር ታውቃላችሁ!)

“ወንድም ቡዝ፣ እውነት ነው፣ የመጽሐፉን ደራሲ ግን በደንብ አውቀዋለሁ።” አልኩት። ስለዚህ፣ እኔ ምፈልገዉ... ታውቃላችሁ፣ ቃሉን ብቻ ማወቅ ሕይወት አይደለም፣ ነገር ግን እርሱን ማወቅ ሕይወት ነው፣ ቃሉን ባውቅም ባላዉቅም፣ እርሱን ካወቅሁ ያ በርግጠኛነት እውነት ነው።

4 ዛሬ ጠዋት በዚህ ጥሩ ህብረት ካላቸዉ አገልጋዮች ጋር ሰላምታ እየተለዋወጥኩ ነበር። እዚህ ተቀምጦ ነበር ....ማንንም ጎልቶ እንዲታይ ለማድረግ ፈልጌ አይደለም፣ ነገር ግን ያ ጎላ ብሎ የሚታየዉ ሰው ግባ፣ ወንድሜ፣ በዚያ ተቀመጥ። በዚህ ላለች ጸሃፊዬ “እዉነተኛ ክርስቲያን አለ” ብዬ ነገሬአታለሁ።

በክርስቶስ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የነበረዉን ሽማግሌዉን ስሚዝን አስታወሰኝ፣ አምናለሁ። እዚያ ብዙ እሰብክላቸው ነበር፤ አሁንም ይህ ሰዉ እርሱን አስታወሰኝ። እዚህ ካለዉ ወንድም ጋር ይመሳሰላል። እሱ ብቻ ግራጫ ጢም ነበረው። በኋላ በር ስገባ አዛውንቱ ይናገር የነበረዉን አነጋገር መቼም አልረሳውም። ወደ ላይ ተመልከቱ፣ ሁሉም ቅዱሳን ይዘምራሉ። አንዲት ትንሽ ልጅ ጥግ ላይ ትቀመጥ ነበር። በጣም የምወደው መዝሙር “ከፍ አድርጉት” የሚል ነበር። ሁሉም ያጨበጭቡ ነበር—ልክ እንደ ጴንጤዎች፣ ታውቃላችሁ—“ከፍ አድርጉት”። እነርሱ ወደዱኝ፣ እኔም ወደድኳቸው። እናም ወደ ውስጥ ስንገባ እርሱ በዚያ ቁጭ ብሎ ጭንቅላቱን ጠረጴዛው ላይ አድርጎ ይመለከታቸው ነበር፣ ታውቃላችሁ፣ “ኮፍያህን አዉልቀህ ግባ ጋሼ፣— ኮፍያዉን አዉልቀዉ” ይለዋል።

5 ይህ ወንድም... እኔ ከምወዳቸው የወንጌል ዘማሪዎች ዉስጥ አንዷ የእርሱ ሚስት እንደሆነች አወቅሁ። እናም እንድትዘምር ለማድረግ የምችለውን ሁሉ ጥረት አድርጊያለሁ። በቸርች በኩል እንዳልጠራት ነገረችኝ፣ እናም ምን ለማለት እንደፈለገች ገብቶኛል። እኔ ግን በግሏ ጋብዛታለሁ። ከቻለች መጥታ ትዘምር።

አንቺ እህት “መርከቤ ሆይ!” ብለሽ የዘመርሽዉ አይደለሽምን? አንድ ቀን ጠዋት በክርስቲያን ነጋዴዎች ህብረት...? ባለቤቴ በዚህ ሳምንት እንደምትነሳ ተስፋ አደርጋለሁ፣ እናም እንድትሰማሽ እፈልጋለሁ፣ ምክንያቱም በጣም ኮራብሻለሁ። በቴፑ ላይ ካጣችሁት እኛ እናስተካክላለን። ያ መዝሙር ጥሩ ነዉ። ወደዋለሁ።

6 ለሰዎች ነግራቸዋለሁ... መቼም መዘመር አልቻልኩም። ወይኔ፣ ከዝማሬ አንድ ሚሊዮን ማይል ሩቅ ነበርኩ። እኔ ግን ለራሴ እንዲህ አልኩ፣ “መቼም በሰማይ ከሄድክና በትልቁ ቤተ መንግስት ውስጥ ብትኖር፣ ታውቃለህ፣ እዚያ ላይ፣” አልኩት፣ “ከኮረብታው ግርጌ ቁልቁል፣ ወደ ጫካው ዉስጥ፣ ወደዚያ፣ ትንሽ ካቢኔ በዚያ ተቀምጧል - ያ የእኔ ይሆናል። አንድ ቀን ጥዋት በረንዳ ላይ ስትወጣ እና አንድ ሰው በዚያ ቆሞ ሲዘምር ስትሰማ፣ 'አስደናቂ ጸጋ! እንደ እኔ ያለዉን ጎስቋላ ያዳነ ድምፁ እንዴት ደስ ይላል! እግዚአብሔርን አመስግኑ ትላላችሁ! ታላቅ ወንድማችን ብራንሃም በመጨረሻ ድል አደረገ።' በዚያ ለመዘመር እየሞከርኩ ያለሁት ያ እኔ ነኝ።

7 ለክርስቲያን ወንድሞቼ እና ለራሴ አምናለሁ፣ አንድ ወንድም ዛሬ ጠዋት ከቡድሃ አገልጋይ አስተዋወቀን ፣ እዚህ ጋር፡ ሰላም ለአንተ፣ ውድ ጓደኛዬ። ከቡድሃ ሰዎች ጋር በተለይም ካናዳ ከሚኖሩ ቻይናውያን ጋር ብዙ ግንኙነት ነበረኝ (በጣም ብዙ አይደለም ነገር ግን ...) በጣም አፍቃሪ እና ጣፋጭ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።

አንድ የቡድሃ እምነት ተከታይ ሰው ከቡድሃ ቤተ መቅደስ ወደ ዊኒፔግ ስብሰባ እንደመጣ አስታውሳለሁ፣ ዓይነ ስውር ነበር። በአካል በጣም ትንሽ ሰዉ ነበር። ጣፋጭ ትናንሽ ሰዎች። በእርግጥም እግዚአብሔር ፈዋሽ እንደሆነ ያምናሉ። እየጸለይኩለት ሳለሁ እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚወድ ደጋግሞ ይናገራል። ወዲያውኑ ዓይኖቹ ተከፈቱ። በጣም አስደናቂ ነገር ነበር። ስለዚህ እያንዳንዱን ሰው እና እያንዳንዱን ግለሰብ እናደንቃለን.

8 ከዚህ በፊት በቺካጎ ይህንን ለመናገር እድል አላገኘሁም፣ ምንም አይነት መልእክት ለማምጣት አልሞከርኩም፣ ምክንያቱም በዚያ ያሉ አገልጋዮች ከእኔ የበለጠ መልእክት ማምጣት ይችላሉ። ደግሞም፣ እዚህ የመጣችሁት መልእክት ለመስማት አይደለም። ነገር ግን የቺካጎ አገልጋዮችን (በዚህ አካባቢ) አግኝቼ ከእነርሱ ጋር የበለጠ መተዋወቅ የምችልበት እና የበለጠ የምንተዋወቅበት ጊዜ በጣም አስደሳች እንደሆነ አስብ ነበር።

ለዚህ እድል ጌታን በእዉነት አመሰግናለሁ፣ ምክንያቱም በአንድ ቤተ ክርስትያን እና በክርስቲያን ነጋዴዎች ስፖንሰርነት ወደ እዚህ ከተማ ብዙ ጊዜ መጥቻለሁ። ቢሆንም ግን ራሴን ለወንድማማች ማኅበር የምገልጽበት ምቹ ሁኔታ አልገጠመኝም። በዚህ “ውጣ ውረድ” በበዛበት አገልግሎት እንደዚህ አይነት ነገር የተለመደ ነዉ። አንዳንድ ጊዜ የተሳሳተ ስሜት ለመሳል ቀላል እስኪሆን ድረስ። እናም በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ነገሩን ለወንድሞቼ ለማብራራት እና ግልፅ ለማድረግ ሞክራለሁ።

9 ለተማሩ ሰዎች የሚሆን ምናልባት የተሻለ ትርጉም የሚሰጥ ንግግር ለማድረግ ብቁ አይደለሁም። ትምህርት የለኝም፣ ያ ይጎድለኛል። ነገር ግን ጌታን እወደዋለሁ፣ እናም ጌታ ነፍሳትን ወደ ንስሃ የምመልስበትን ሌላ መንገድ ሰጠኝ—መለኮታዊ ስጦታ — ወላጆቼ ሊሰጡኝ ያልቻሉትን ክፍተት ለመሙላት- የትምህርትን ቦታ ሞላልኝ። ከድሃ ቤተሰብ፣ አሥር ልጆች፣ ታማሚ አባት፣ እናም ከዚህ የተነሳ የመማር ዕድል አላገኘሁም።

ስለዚህ...ነገር ግን በዉልደቴ ጊዜ አንድ ነገር ሆነ - እናቴ እና አባቴ ከእግዚአብሔር ጋር ተነካኩ (ታሪኬን አንብባችሁታል) እና በዚህም ከእናንተ ወንድሞቼ ጋር በመሆን ኃጢአተኞችን ወደ ክርስቶስ ለመሳብ ሞክራለሁ።

10 አሁን፣ እኔ አጉል እምነት የለኝም፣ ግን ሁልጊዜ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከመክፈቴ በፊት፣ የቃሉን ደራሲ በጥቂቱ ማናገር ወዳለሁ። ለትንሽ ጊዜ እንደገና ከአንገታችን ዝቅ ማለት እንችል ይሆን?

ውድ አባታችን ሆይ አንተ አምላካችን ነህ፣ በወንጌል በኩል ወደ አንተ እንቀርባለን። አሁን እኔ በልጆችህ፣ በመጋቢዎችህ፣ እና በዚህ ውድ እምነት አማኝ ወንድሞች ፊት አለሁ። ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ስለተረዷቸዉ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ ወደ ተቋማት የተላኩትን ሰዎች ምስክርነት ስሰማ ልቤ ይነካል። በመጨረሻው ዘመን ልጆችህን እንዴት እንደምትጠራ ተመልከት። እናም አባት ሆይ በእውነት እናምናለን፣ በውድድሩ ዘመን መጨረሻ ላይ እየኖርን ነው። ነቢዩ እንዳለው "በመሸ ጊዜ ብርሃን ይሆናል"፣ እናም እኛ ዛሬ የዚህ ታላቅ የወንጌል ብርሃን መልእክተኞች መሆናችንን በማመን በጸጋህ አማካኝነት ይህ መነቃቃት ወደ ደረሰበት እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንድናደርስ ፈቀድክልን።

እናም አባት ሆይ፣ በዚህ ማለዳ ላንተ ያለኝን የልቤን ሃሳብ እና አላማ ለወንድሞቼ እንድገልጽ፣ እነርሱም ደግሞ እንዲረዱ እንድታርግ ጸልያለሁ። በወንጌል ስራ ሁሉ ፍፁም ፍቅር ፣ ህብረት እና ትብብር እንዲኖረን ስጠን። እርሱና አባቱ አንድ እንደሆኑ እኛም አንድ እንሆን ዘንድ በጸለየው በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። "... እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፣ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች በዚህ ያውቃሉ።" የሚለዉን ቃል በማመን፣ አሜን።

11 አሁን በዚህ ላይ ወንድሞች እና እህቶች እንዳላሰለቸኳችሁ ተስፋ እና እምነት አለኝ፣ ነገር ግን ከሌላ ሰው የሚያወራዉን እንዳትሰሙ ራሴን ግልጽ ማድረግ ያለብኝ ይመስለኛል። በሌሎች የአገልጋዮች ስብሰባዎች ላይ ብዙ ጊዜ አብራርቻለሁ፣ ነገር ግን ለቺካጎ ቡድን ይህ የመጀመሪያዬ ነው፣ እና ምን ለማድረግ እየሞከርኩ እንዳለሁ ግልጽ ማድረግ ፈልጋለሁ።

12 በተባረከው የጥንቱ ወንጌል፣ የሐዋርያትሥራ መጽሐፍ፣ ሃያ ስድስተኛው ምዕራፍ ላይ እንዲህ እናነባለን።

ስለዚህ፥ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፥ ለሰማያዊው ራእይ እምቢተኛ አልነበርኩም።

ይህ የጳውሎስ ንግግር ነው - እኛ ሁላችን እንደ አገልጋይ እርሱን መጥቀስ እንወዳለን ምክንያቱም እኛ በአንድ ልብ እርሱ ለአሕዛብ ምስክር እንዲሆን እግዚአብሔር የጠራዉ የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ እንደሆነ እናምናለን። አገልግሎቱም ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ነበር። ብዙውን ጊዜ፣ ማንኛዉም ያልተለመደ ነገር ብቅ ሲል፣ ጥያቄ ዉስጥ ይገባል፣ እናም ትክክለኛ አይደለም ሳይሆን የሚባዉ ጥያቄ ይነሳበታል።

እና ፓስተሮች አንዳንድ ጊዜ በሚሰሙት ነገር ይጠራጠራሉ፣ የመጠራጠር መብት ያላቸው ይመስለኛል። ምክንያቱም 'ፓስተር' የሚለዉን ቃል ትርጉም በትክክል ከተረዳችሁ፣ "እረኛ" ማለት ነው፣ ስለዚህም እርሱ መንፈስ ቅዱስ የበላይ አድርጎ የሾመው የወንዶችና የሴቶች ቡድን መጋቢ ወይም እረኛ ነው። በጎቹም ምን አይነት ምግብ እንደሚያገኙ እና ከየት እንደመጣ የማወቅ መብት አለው። ለዚህም መብት ያለው ይመስለኛል። ፓስተር፣ ወይም አንዳንድ ጊዜ ሌሎች ሰዎች፣ ትንሽ የሚጠራጠሩ ቢመስሉ፣ ያ በጭራሽ... ማንንም ሊያስጨንቅ አይገባም። ለዚያ አቋም ላለው ሰው ልብ ክብርን ከማምጣት ባለፈ ጥያቄ ሊሆን አይገባም።

13 ደግሞስ፣ በትክክለኛ መስመር ላይ መሆንህን እርግጠኛ ካልሆንክ እንዴት በእምነት መጓዝ ትችላለህ? አእምሮህን ካሳመንክ.... አሁን፣ ይህ ሳይኮሎጂ ሊመስል ይችላል፣ ከሆነም ይሁን። ምንም አይደለም። ነገር ግን ከልብህ ከጠረጴዛ ላይ በጭራሽ እንደማትነሳ ብታስብ በቃ ላትነሳ ትችላለህ። አያችሁ....ተረዳችሁ....ያን ያህል ቀላል ነው። ማመን አለባችሁ። እምነት ሊኖራችሁ ይገባል፣ በራሳችሁ መተማመን አለባችሁ።

እናም ወዴት እንደምትሄዱ እንኳን በአግባቡ ሳታዉቁ በማንኛዉም ነገር ላይ እንዴት በራስ መተማመን ሊኖራችሁ ይችላል? ከዚህ በፊት ተጉዤበት በማላዉቀዉ መንገድ እንዴትበፍጥነት ላሽከረክር ችላለሁ? ጠመዝማዛ መንገዶችን? ቀጥሎ ባለዉ ጠመዝማዛ መንገድ ምን እንደሚገጥመኝ በማላዉቅበት ሁኔታ? ወዴት እንደምትሄድ ማየት አለብህ፣ አለበለዚያ እንዴት መሄድ እንዳለብህ አታውቅም። እናም ሁሉም ሰው እንደዚህ መሆን አለበት። ከዚያም ባየኸው ጊዜ ይገለጥልሃል፣ ወዴትም እንደምትሄድ ታውቃለህ፣ ከዚያ ማንም ሊያቆምህ አይችልም።

14 እናም ያ ነው... እኔ እንደማስበው፣ ጳውሎስ ለአግሪጳ ለማስረዳት የሞከረው ይሄንን ነዉ "በአንድ ወቅት ከእናንተ እንደ አንዱ ነበርኩ" ብሎ ነገራቸው። እናም ይህ ባፕቲስት ወንድም እና ሚስቱ ዛሬ ጠዋት ወደ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን መሄድ ከቻሉ ይህ ምናልባት ምስክርነታቸው ሊሆን ይችላል፡ "በአንድ ወቅት ከእናንተ እንደ አንዱ ነበርኩ"። ወይም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወይም ደግሞ እዚህ ያለው የካምቤል ወንድም ወደ ህዝቡ ይሄዳል....(በተሻለ ስም እንደሚጠራ አምናለሁ። የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ብለዉይጠሩታል። ግን ነገሩ በትክክል የአሌክሳንደር ካምቤል ዶክትሪን ነዉ። ከዚያም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በሙዚቃ ምክንያት ከእንተ ወጣች። ያ ትክክል ነዉ።) እናምተመልሶ ወደ እነርሱ መሄድ ከቻለ "በአንድ ወቅት ከእናንተ እንደ አንዱ ነበርኩ" ይላል።

15 ጳውሎስም ወደ ንጉሡ ወደ አግሪጳና ወደ ፊስጦስ ተመልሶ እንዲህ አላቸው "በአንድ ወቅት ከእናንተ እንደ አንዱ ነበርኩ። ከፈሪሳውያንም ፈሪሳዊ ነበርኩ"። በታላቁ መምህር ገማልያል እግር ሥር ተቀምጦ ሕግ እና ሥርዓቶቻቸውን ሁሉ ተምሯል። የሚያምኑትን እና የማያምኑትን ነገር ሁሉ ያውቃል። እንዲህም አለ፣ "የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እስከ ሞት ድረስ አሳድጄ ነበር፣" አያችሁ። "ዋና የተከሰስኩበት ነጥብ አሳዳጅነቴ ነዉ" አለ።

የእስጢፋኖስ ሞት በጳውሎስ ላይ መድረስ ነበረበት ብዬ ብዙዉን ጊዜ አስብ ነበር፤ ምክንያቱም ያን የከበረ የእስጢፋኖስን ፊት ሲያይ፣ እስጢፋኖስ ቀና ብሎ ወደ ሰማይ ሲመለከት፣ እስከ ሞት ድረስ ሲደበድቡት፣ "ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየሁት" አለ። ታውቃላችሁ፣ መልእክተኛን ልትገድሉ ትችላላችሁ፣ መልእክቱን ግን በፍጹም መግደል አትችሉም። ምንም እንኳን እስጢፋኖስ ወደ ኢየሱስ ቢሄድም መልእክቱ ግን ጸንቶ ነበር። ምክኒያቱም ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ ዙርያ መናገርቀጥሎ ነበር። ከሁሉ ታናሽ ነበረ። ከእነርሱም እንደ አንዱ ሊቆጠር አይገባዉም ነበር። ምክኒያቱም ይህ የእግዚአብሔር ሰዉ ይገደል ዘንድ ምስክርነቱን እና ፈቃዱን ሰጥቶ ነበር።

16 ስለዚህ ጳውሎስ ከእርሱ በፊት የነበሩት ሰዎች ያደርጉት እንደነበረዉ ሁሉ ከመጀመሪያው አንስቶ አሁን እስካለበት ድረስ የነበረዉን ልምዱን ከቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶች ጋር በማያያዝ ያደርጋቸዉ የነበሩት ነገሮች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የተፃፉ ጥቅሶች መሆናቸዉን ያሳያል። ከእምነታቸው ጋር የሚቃረን ቢሆንም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች እያጣቀሰ ያሳያቸው ነበር። ስለዚህ ስብሰባዎችን የተሳተፋችሁ ወንድሞች፣ ብዙ ጊዜ እንዳልኩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ነገሮችን ስናገር ከሰማችሁ እርስ በርሳችን በመቀራረብ “ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም” ልንል ይገባናል። አያችሁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ ከሆነ ግን የተለየ ትርጓሜ ወይም እይታ ሊኖረን ይችላል፣ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከሆነ ግን ምንም ማድረግ ወይም መለወጥ አይቻልም።

17 አሁን ጳውሎስ፣ ነቢዩ እና ሙሴ የተናገሩት ትንቢት እንደተፈጸመ የሚያሳይ ትርጓሜ እየሰጠ ነዉ። በመንገድ ሲጓዝ ኢየሱስን በራዕይ አገኘው። በዚህም ኢየሱስ ወደ እርሱ ጠራው... ለእነዚያ አይሁዶች ከባድ ነገር አልነበረም። “ክቡር ፊስጦስ” እና ሌሎቻችሁም “እግዚአብሔር ሙታንን ማስነሳቱ ይገርማችኋልን? አምላክ የሰራዉን እና በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈዉን ካወቃችሁ እርሱ ሙታንን እንደሚያስነሣ ታውቃላችሁ።”

ይህ ጳውሎስ የሚሰብከዉ እነርሱ ግን የተቃወሙት ኢየሱስ ሁልጊዜም ያገለግሉት የነበረው እዉነተኛዉ አምላክ እርሱ እንደ ሆነ እንዲያውቁ ለማድረግ በደማስቆ መንገድ ላይ የገጠመዉን ነገራቸዉ። እርሱ “ኢየሱስ” ከእነርሱ ጋር በምድረ በዳ ነበርና፥ የመራቸውም ብርሃን፥ እሳት፥ የእሳት ዓምድ ነውና። ለጳውሎስም እንዲሁ ከባድ ብርሃን ታየው-አሳወረው።

እናም እንዲህ ብሎ ጠየቀ፡- “ጌታ ሆይ፥ አንተ ማን ነህ?”

እርሱም፡- “አንተ የምታሳድደኝ፣ እኔ ኢየሱስ ነኝ። የመዉጊያዉን ብረት ብትቃወም ላንተ ይብስብሃል።” አለዉ።

18 ነገሩ ምን እንደሆነ ሊገልጽላቸዉ እየሞከረ ነበር። እናም ያ ነገር ምን እንደሆነ ሊያስተምራቸው እየሞከረ ነበር? ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሕ መሆኑን ለሰዎች እያስረዳ ነበር፣ እርሱም እንደ ሞተ፥ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ ወደ እግዚአብሔር አብ ወደ ላይ እንዳረገ፣ እናም ጳዉሎስ የትንሣኤው ምስክር እንደ ሆነ። በሕዝብ ሁሉ ፊት እንግዳ የሆኑት እነዚህ ተአምራት፣ ምልክቶች፣ ድንቅ ነገሮች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለተናገረ ለእውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አማኝ አዲስ ነገር አልነበረም።

19 የመሲሑን መምጣትና ከመጣም በኋላ የሚሰራቸዉን ስራዎች በትንቢት እንዴት እንደተተነበየ በነቢያት መጽሐፍት ላይ ተመልከት፡ አንካሶች እንደ ዋላ ይዘላሉ(ኢሳይያስ 35) ሌሎችም ሊጠቅሳቸው ይችል የነበሩ የተለያዩ ጥንታዊ ጥቅሶችን መጥቀሱ አይቀርም። በርግጥ እዚህ ላይ ተጽፎ አይገኝም፤ ነገር ግን ምናልባት በነገሥታቱ ፊት ባቀረበው አጭር ንግግሩ ላይ ወደ ኋላ ሄዶ ጥቅሶችን ባያቀርብ ኖሮ እናንተ እኔን እንደታገሳችሁኝ እነርሱ አይታገሱትም ነበር።

ከዚያም እነርሱ የሚያገለግሉትን እዉነተኛዉን አምላክ እየገለጠላቸዉና ሊነግራቸው እየሞከረ...እንደገናም እነርሱ “ይህ መናፍቅ እብድ ነው” ብለዉ በሚጠሩት መንገድ እግዚአብሔርን እንደሚያመልክ ነገራቸዉ። አያችሁ “መናፍቅ” ተብሎ በሚጠራዉ መንገድ።

ርግጠኛ ሆኜ የምነግራችሁ እኛም ዛሬ ቀድሞ ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ማለትም እንደ ፕሪስቢቴሪያን፣ ካቶሊክ፣ ባፕቲስት እና ሌሎች ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ሸንጎ ፊት ብንቆም ልክ እንደ ጳዉሎስ ተመሳሳይ ምስክርነት እንሰጣለን...በሳይኮፓቲክ ዋርድ ውስጥ ያለ ወንድም፣ ወይም እንደዚህ ያለ ነገር። “የአባቶቻችንን አምላክ የማመልከው መናፍቅ በምትሉት በዚህ መንገድ ነው።”

20 እንዴት ያለ ታላቅ ምስክርነት ነው፣ አግሪጳም በጳውሎስ ንግግር መካከል ጮኸ፣ “ጳውሎስ...ሳውል፣ ክርስቲያን እንድሆን ልታሳምነኝ ትንሽ ቀረ!” ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዴት አድርጎ እንደ ተናገረ ተመልከቱ፤ ነገር ግን ከገዛ ምኩራቡ ጋር ይቃረናል፤ “አንተን እንድመስል ልታሳምነኝ ትንሽ ቀረ!” እስኪል ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍት ፍጹም ግልጽ ነበሩ።

ጳውሎስ እንዲህ አለ፡- “ከዚህ ሰንሰለት በስተቀር ሁላችሁም ልክ እንደ እኔ ብትሆኑ ደስ ባለኝ ነበር...እኔ ባለሁበት ሰንሰለት እንድትኑ አልፈልግም፣ ነገር ግን ልክ እንደ እርሱ አማኝ እንድትሆኑ ይፈልጋል። በሌላ አነጋገር፣ ”እኔ ያየሁትን የእግዚአብሔር ራዕይ ብታዩ እመኛለሁ። እንዲህ ማድረግ ብትችሉ እመኛለሁ። እንድታደርጉ ብቻ እመኛለሁ።“ አምናለሁ።

ፊስጦስ ብዙ እንዳጠና ሲነግረው በጭንቅላቱ ወድቆ ነበር። ጳውሎስ ግን እንደማያዉቅ አሳወቀው። የት እንዳለ አሳወቀው።

21 እናም ዛሬ ማለዳ፣ ወንድሞች ሆይ ፣ ይህን እላለሁ። በአጠቃላይ እፈጽም ዘንድ እመኛለሁ.... የጳውሎስን ሕይወት ሳይሆን፣ ትንሽ መሠረታዊ ንግግር ለመናገር ብቻ ነው፣ ምክንያቱም ምናልባት ይህንን የሚናገሩ ሌሎች ብዙ ሰዎች በዚህ ማለዳ እዚህ ይኖራሉ። ግን ይህን ለማለት እድሉን ፈልጌ ነበር። አሁን በዚህ መደዳ ያሉ እያንዳንዱ የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት፣ ቤቴል፣ ገለልተኛ፣ ጉባዔ እግዚአብሔር እና ሌሎች የተለያዩ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ - የማየውን ማየት እንድትችሉ እመኛለሁ። የማየውን ራዕይ እንድታዩ እመኛለሁ። ከዚያም ስለዚህ አገልግሎት የበለጠ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ይኖራችኋል።

22 ከባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ወጥቼ ወደ ጴንጤቆስጤ ስመጣ፣ በባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን በሚሲዮናዊነት የሾመኝ ዶ/ር ሮይ ኢ. ዴቪስ፣ ጌታ በራዕይ ያናገረኝ ቅዠት እንደሆነ ነገረኝ። በዚያን ጊዜ ፈውስ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነበር። ስለ ጴንጤቆስጤዎች ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም። ወለል ላይ ተዘርግተው ልክ እንደ እብድ ውሾች የሚያጓሩ የቅዱሳን ተንከባላዮች ስብስብ መሆኑን ሰማሁ እናም እነሱን ማራገብ እና ወደ ህይወት መመለስ ነበረባቸው እና ሁሉም እንደዚያ። ስለ ጴንጤቆስጤ ሰዎች የማውቀው ይህን ብቻ ነው።

እርሱም “ማን የሚሰማህ ይመስልሃል?” አለኝ።

“የላከኝ እግዚአብሔር ከሆነ የሆነ ቦታ የሆነ የተላኩለት ሰው አለ” አልኩት። ልክ ነው። አያችሁ እኔም “ዶ/ር ዴቪስ አልኩት” ፣ “እርሱም እንዲሁ እውነተኛ ነበር። ፊት ለፊቱ ቆሜ ተመለከትኩት። ”እነዚያ ራእዮች ነገሩኝ...“ አልኩት።

23 ወንድሞች ሆይ እኔ ታላቅ አማኝ ነኝ። የጸጋ ስጦታዎች እና ጥሪዎች ከንሰሃ ውጪ ናቸው። እግዚአብሔር በስጦታዉ አይጸጸትም። ያንን አምናለሁ። ተወልዳችኋል... ያልሆናችሁትን መሆን አትችሉም። ያልሆናችሁትን ለመሆን ስትሞክሩ የግብዝነት ሚና እየተጫወታችሁ ነው። እናም እግዚአብሔር ሆይ ግብዝ ከመሆኔ በፊት ልሙት። እኔ የሆንኩትን ብቻ ልሁን፣ ከዚያም ግልጽ እና ግልጽ ሆኜ በዚያ መልኩ ልገኝ። ከዚያም ሁሉም ሰው ያውቃል። እናንተም በትክክል ታዉቃላችሁ።

እናም አሁን፣ እንደምታውቁት፣ ብዙም በትምህርት አልገፋሁም። እንደነገርኳችሁ በሥነ መለኮት እዉቀት በጣም ድሃ ነኝ። ያንን እንደምታዉቁ ገምታለሁ። እናም እንደ ሰባኪ፣ ትምህርት ባለማግኘቴ እና ቃላትን ስለማላዉቅ ራሴን ሰባኪ ብሎ ለመጥራት ይከብደኛል። ነገር ግን ያለኝ ትንሽ ነገር በጸጋው የጌታ ኢየሱስ እውቀቴ ነው። ይህን እዉቀት በየቦታውላሉ ወንድሞቼ ለማካፈል ሞክራለሁ።

24 እኔ ግን ከመጀመርያ ጀምሮ የነበርኩበት እና የተሾምኩበት ብቸኛ ቤተ ክርስቲያን ከሆነው ከባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ስወጣ....የተሾምኩት እእአ በ1933 በጀፈርሰንቪል ኢንዲያና በሚሲዮናዊ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ነበር። ቤተ ክርስቲያኗ የደቡብ ባፕቲስት ኮንቬንሽን አባል ነበረች። የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊት ቤተ ክርስቲያን ነች። ሁላችንም እናውቃለን። ጉባኤዉ የሚቀበላችሁ ከሆነ ስለምትፈልጉት ነገር ሁሉ መስበክ ትችላላችሁ። የፈለከውን መስበክ ትችላለህ። እኔም ወድጄዋለሁ፣ እነሆ፣ ሐዋርያዊ ነው ብዬ ስለማምን ነው፣ ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሃላፊነት እረኝነት ነው። ያንን እንገነዘባለን - ፓስተር። እናም አንዳንድ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ሌላ ሰው ከመጋቢው ራዕዩን ሊጋፋ ከሞከረ፣ ታዲያ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዴት ይሰራል? አያችሁ። የማይሆን ነገር ነዉ።

25 ስለዚህ ከዚያ ስወጣ ከመጀመሪያው ቡድን ጋር ተገናኘሁ፣ እሱም በሴንት ሉዊስ፣ ሚዙሪ የትንሺ ቤቲ ዳገርቲ ፈውስ ነበር። የተባበሩት ጴንጤቆስጤ ወይም የጴንጤቆስጤ የኢየሱስ ስም ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ነበር። እናም ትንሽ ሴት ልጁ ተፈወሰች። እውነት ለመናገር እርሱን ጴንጤ ያደረገው ይህ የህጻኗ ፈዉስ ይመስለኛል። ራሳቸውን "ኢየሱስ ብቻ" ብለው በመጥራታቸው ነው ብዬ አስቤ ነበር። ጴንጤ ያደረጋቸውም ይህ ነው ብዬ አሰብኩ ምክንያቱም ልዩነቱ እነሱ እራሳቸውን የሚጠሩት እንደዚያ ነው።

ከዚያ ወደዚያ ሄድኩ.... እናም ጥሩ ሰው ነበረ። በሴንት ሉዊስ ታላቅ ስብሰባ ነበረው (ምስሉ እዚያ ላይ ይታያል)። የኪየል አዳራሽ ነበረን ፣ እናም በመጀመሪያ ወይም በቀጣይ ሁለት ምሽቶች ፣ አሥራ አራት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ታጭቀው ነበር። አልቻልንም ነበር ... ሰዎችን ለማራቅ ፖሊሶችን በሮች ላይ ማስቀመጥ ነበረብን።

26 እናም ከዚያ ወደ ታች የዚሁ ድርጅት ተመሳሳይ የነበረው በጆንስቦሮ የሚገኘው ቡሩክ የብሉይ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዓት ድንኳን ሪቻርድ ቲ.ሪድ ከዚያም ወደ ዶ/ር ጂ ኤች ብራውን, ተመሳሳይ ድርጅት በ 505 ቪክቶር ጎዳና በሊትል ሮክ አርካንሳስ እናም ከዚያ ደግሞ ወደ ምዕራብ የባህር ዳርቻ።

እናም ከዚያ ወደ ምእራብ ጠረፍ ስደርስ እሳቱን አገኘሁት። ከዚያም ልክ እንደ እኛ ባፕቲስቶች በድርጅታቸው ውስጥ በጴንጤቆስጤ ሰዎች መካከልም ብዙ መከፋፈል እንዳለ ተረዳሁ። በጣም ብዙ የተለያዩ ነበሩ....የተለያዩ ነበሩ....ጉባዔ እግዚአብሔር ነበሩ፣ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፣ እና ሌሎችም፣ ልዩነት ነበረ። ተለያይተው በመካከላቸዉ ትንሽ ድንበር ዘርግተው ነበር። ሁሉም ወንድሞች ወደ እኔ መጥተው፣ "ለምን አንተ ከዚህ ቡድን ጋር 'ኢየሱስ ብቻ' ሆንህ" ይሉኝ ጀመር።

"አይ፣ ራሴን እንደዚያ አልጠራውም" አልኳቸዉ።

እርሱም "ለምን ራስህን ከእነርሱ ጋር ታዛምዳለህ" አሉኝ።

እኔም "ወንድሞቻችን ናቸዉ" አልኳቸዉ።

እርሱም "ስብስብ ናቸው....ምንም የላቸውም ከትንሽ መንጋጋ እና መሰል ነገሮች በስተቀር።"

እኔም "አሁን ይቅርታ ጠይቃለሁ። እዚያ እውነተኛ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውን ሰዎች አገኛለሁ፣ እነርሱም የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው።" "ሌሎች በከፋት ሲጠሯቸዉ እቃወማለሁ" አልኳቸዉ።

27 እንግዲህ የሁለቱንም መንገድ ሳልገልጽ እስከምችለው ድረስ ለማቆም ሞከርኩ። ሃሳባቸው ምን እንደሆነ፣ መለያየታቸውስ ምን እንደሆነ፣ እንዲለያዩ ያደረጋቸውንም ነገር ማጥናት ጀመርኩ። እናም ከታላላቅ ቡድኖች ሁለቱ አንዱ ዋንነስ ወይም ኢየሱስ ብቻ ተብሎ ሲጠራ ሌላኛው ደግሞ ጉባዔ እግዚአብሔር ተብሎ ይጠራ ነበር። የተለያዩበት ጉዳይ አንደኛው የዉሃ ጥምቀት "በአብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም" መሆን አለበት ሲል ሁለተኛው ደግሞ "በኢየሱስ ስም" በሚል ነው።

ሁሉንም ተመለከትኩ፣ እናም በሁለቱም በኩል ታላላቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነበሩ። አሰብኩ፣ "አምላክ ሆይ፣ ሁሉም አንድ ቢሆኑ ኖሮ ... በቃ ቀጥልበት.... ነገር ግን 'እርስ በርሳችን አንገናኝም' እያሉ መስመር ማስመራቸዉን ቢያቆሙ።" ነገር ግን በዚህ ውስጥ እርኩስ መንፈስ በመካከላቸው እንደገባ እና በመካከላቸው በመጡ ጉዳዮች ላይ ጥላቻ እና ክፋት እንዳስከተለ ተረዳሁ። አሰብኩ፣ "ይህ ዲያቢሎስ የሚፈልገው ነው። እርሱ የሚፈልገው ብቻ ነው። ሽጉጣችሁ እርስ በርሱ እስከሰለጠነ ድረስ ምላሱን መዋጋት የለበትም።"

በመጨረሻም ወደ ትርኢት መጣ። እናም ትርኢቱ በሲያትል፣ ዋሽንግተን በ1946 ገደማ ነበር።

28 አንድ ቀን ጠዋት ከተወሰኑ አገልጋዮች ጋር ቁርስ ለመብላት ወደ ሆቴል አዳራሽ ሄድኩ። ሁለት ዋና ሰዎችን ማነጋገር ነበረብኝ። አንዱ ዶ/ር ኔስ ነበረ። ከጉባዔ እግዚአብሔር የመጣችሁ ወንድሞች የምታስታዉሱት ይመስለኛል። የሰሜን ምዕራብ ግዛት ነበር። ታላቅ ሰው፣ ብልህ፣ ምሁር፣ እናም እሱ የእግዚአብሔርን ጉባኤዎች ወክሎ ነበር። ሌላኛዉ ደግሞ ዶ/ር ስኪዝም ከተባባሩት የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን። ከተባበሩት ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን የመጣችሁ ወንድሞች እንደምታስታዉሱት ገምታለሁ። እሱም ደግሞ በዚያ የሰሜን ምዕራብ ግዛቶች.... እና በአውራጃዎች ላይ ነበር።

እነዚህ ሁለት ሰዎች ተገናኙ፣ እናም እኔ ፊታቸዉ ልቀርብ ነበር፣ ምክንያቱም ጠርዙ ስለታም ነበር፣ ከሁሉም አቅጣጫ ይቆርጠኝ ነበር።

እኔም "ምን ማድረግ አለብኝ? ምን ላድርግ?" ብዬ አሰብኩ።

29 አሁን..."እሺ" አሉ፣ "ከአንዱ ወይም ከሌላው ጋር መወገን አለብህ። በዋንነስ መንገድ የምትሄድ ከሆነ የዋንነስ መሆን አለብህ። ከጉባዔ እግዚአብሔር ጋር ከቀጠልክ ከዋንነስ ወጥተህ ጉባዔ እግዚአብሔር መሆን አለብህ።" የሆነ ዉሳኔ መወሰን እንዳለብኝ ቁርጥ ቦታ ደረሰ። ያን ቀን ጠዋት ከእነርሱ ጋር ከመገናኘቴ በፊት ብዙ ጸልዬ ነበር። እኔም "እግዚአብሔር ሆይ፣ እርዳኝ፣ ምክንያቱም ሁለት ታላላቅ ሰዎች አሉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ አገልጋዮች አሉ፣ ወደዚህ ለአገልግሎት ልከኸኛል። ሁለቱም የአንተ አገልጋዮች ናቸው፣ አንዱ ድርጅት ሌላውን ሲዋጋ ሳይ ያለችኝን ትንሽ

ተፅዕኖ ልወርውር ወይስ ልተዉ?" አያችሁ? "ይህ ትክክል መስሎ አልተሰማኝም። ይህን ላደርገው የክርስቶስ ፈቃድ አልመሰለኝም።" "እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ። የምሰራውን ነገር ወይም የምናገረውን ስጠኝ" አልኩት። እናም ከዚያ ማንም አልነበረኝም። በዚያ መቆም ነበረብኝ። ጌታ ኢየሱስ እና እኔ ብቻ በዚያ ጠዋት።

30 እንግዲህ ታላቁ ክርክር መጣ። "በቀጣይ ምንድነው የምታረገው? ምን አይነት ዉሳኔ ትወስናለህ?"

እኔም "ውሳኔዬ አስቀድሞ ተወስኗል። ውሳኔዉም በሁለታችሁም መሀል መቆም፣ የትኛውንም ድርጅት አለመቀላቀል እና ሁለታችሁንም አቅፌ፣ 'እኛ ወንድማማቾች ነን። ወንድማማቾች ነን!'" ማለት ነዉ። እናም እንዲህ አልኩ "በዚህ ዙሪያ ማንበብ የቻልኩትን መጽሃፍቶች ሁሉ ለማንበብ ሞክሬአለሁ። ይህ ጉዳይ እንዴት እንደመጣ፣ ይህ 'አዲስ ጉዳይ' ተብሎ የተጠራዉ፣ እንዴት ራሳቸውን እንደሚለያዩ እና መለያየቱ በዚህ እና በዚያ መንገድ እንዴት እንደጀመረ ለማንበብ ሞክሬአለሁ።" እናም እንዲህ አልኳቸዉ "በእናንተ መካከል የተነሳዉ ክርክር፣ ያ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ የነበረውን የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ ያፈረሰው ይኼው ነው። እርስ በርሳቸው መከራከር ጀመሩ፣ እናም በዚህ መልኩ ልዩነት ይፈጠራል። በእናንተ ወንድሞች መካከል የሚያቀራርብ ወይም የሚያስታርቅ ሚዲያ ሊኖር የሚችልበት ዕድል ካለ" ብዬ ጠየኳቸዉ።

ለዚህ ነጥብ መልስ አልሰጡም። ዝም አሉ። ምክንያቱም ጥያቄዉ በጣም ስለታም ነበር። የዛሬ አስራ አምስት፣ ሃያ አመት አካባቢ እንዴት እንደነበረ ታዉቃላችሁ፣ አንዱ ቡድን ከሌላው ገንጥሎ ይወጣል። በጣም ጠብ ነበር።

31 ስለዚህ እንዲህ አልኳቸዉ "ወንድሞች ሆይ፣ እኔ የማደርገው ይህ ነው፣ እኔ ሄዳለሁ... አምላክ ፈጽሞ ለማጥመቅ አልላከኝም፣ የላከኝ ለታመሙ ልጆቹ እንድጸልይ ነዉ። ስለዚህ እኔ ለታመሙ ልጆች ጸልያለሁ፣ እናንተ አገልጋዮች የጥምቀቱን ስራ ስሩ።"

ነገሩን እንድትረዱት "አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ ፈልጋለሁ።" አልኳቸዉ። እኔም፣ "ወንድም ኔስ፣ እነዚህ የዋንነስ ሰዎች፣ በልሳኖች ሲናገሩ እና አንተ በጉባኤ እግዚአብሔር ውስጥ የምታደርገውን ነገር ሲያደርጉ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ታምናለህ?" አልኩት።

እርሱም፡- "በእርግጥ" አለ።

እኔም፣ "ወንድም ስኪዝም፣ ጉባዔ እግዚአብሔር በልሳኖች ሲናገሩ እና በዉሃ ጥምቀት ላይ ያደረግከውን ተመሳሳይ ነገር ሲያደርጉ መንፈስ ቅዱስ እንዳላቸው ታምናለህ?"

እርሱም "በእርግጥ" አለ። "መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሚታዘዙት መንፈስ ቅዱስን ይሰጣል" ይላል። እናስ አሁን የታዘዘው ማን ነው? እሱን የታዘዘው ማን ነው? ከእናንተ የሚታዘዘው ማን ነው? እግዚአብሔር ለእናንተ ለሁለታችሁ መንፈስ ቅዱስን ሰጥቷል? ተመልከቱ፣ "ወንድም ስኪዝም፣ ወንድም ኔስ መንፈስ ቅዱስን አልተቀበለም ትላለህ?" አልኩት።

እሱም "በፍፁም" አለ።

እኔም "ወንድም ኔስ፣ ወንድም ስኪዝም መንፈስ ቅዱስን አልተቀበለም ትላለህ?" አልኩት።

"በፍፁም" አለ።

አያችሁ...ሁለቱም እርስ በርሳቸው የሚያምኑት መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ነው። ግን አያችሁ ወንድሞቼ ሆይ ምንም ትርጉም የለውም። ትርጉም የለውም።

32 ከዚያ ትንሽ ቆይታ በኋላ ሰማሁ....(ከአንድ ደቂቃ በኋላ ወደ ነጥቤ እመለሳለሁ)።

በፊንላንድ እኔ እንደማስበዉ እስከዛሬ ካደረግናቸዉ ስብሰባዎች ታላቅ ሊባሉ የሚችሉ ስብሰባዎቻችን እንድናደርግ እግዚአብሔር ረዳን። በዚያም የሞተ ልጅ ከሞት ተነሣ። ሌሎች ብዙ ድንቅ ነገሮች ሆኑ... ፊንላንድን ለቅቄ ከወጣሁ በኋላ በስቶክሆልም ስዊድን አሁን በዚህ ካሉት የፊንላንድ ወንድሞች የፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከሆነዉ ከሊዊፔትረስ ጋር ተገናኘን። ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነው። ሌላዉ የፊላዴልፊያ ቤተ ክርስቲያን ....ወንድም ጎርደን ሊንሴይ፣ አሁን በዚያ ያለ አይመስለኝም... በፊት ግን እዚያ ነበር... አሁን የጉባዔ እግዚአብሄር አባል ነዉ። እናም ጉባዔ እግዚአብሄር በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ታላላቅ ስፖንሰሮቼ መካከል አንዱ ነው። ከጉባዔ እግዚአብሄር የወጣዉ ፎርስኲዌርም ከታላላቅ ስፖንሰሮቼ መካከል አንዱ ነው። ዋንነስም እንዲሁ።

እናም አሁን የሾሉ ጠርዞችን ትቼ ገለልተኛ አቋም ያዝኩኝ። ወደ አንድነት መምጣት እና ወንድማማቾች መሆናችንን ማወቅ እስክንችል ድረስ ከሁለቱም ወገን ገለልተኛ መሆን እንዳለብኝ አሰብኩ። ከዚያም ሁላችንም ወደዚያ የምንመጣበትን ተመሳሳይ እና ቀጥተኛ ነጥብ ማለትም ተነሳሽነት እና አላማ እንመለከታለን።

33 መጀመሪያ የልብህን መሻት እና አላማህን መፈተሽ አለብህ። ከሁሉ አስቀድመህ የአምላክን ፈቃድ እሻ፣ ከዚያም ዓላማህን እወቅ፣ ከዚያም የልብህን መሻት ፈትነህ መሻትህ ትክክል መሆኑን ተመልከት። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማርቆስ ፲፩:24 እንደተናገረው "በልብህ ሳትጠራጠር ይህን ተራራ 'ተነቅለህ ወደ ባህር ግባ' ብትሉት...." ነገር ግን በልብህ እስከተጠራጠርክ ድረስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን፣ ወይም መሻትህ ወይም ዓላማህ ትክክል ቢሆን ተራራዉ እንዴት ሊንቀሳቀስ ይችላል? ነገር ግን መሻትህ ትክክል ከሆነ እና የእግዚአብሔር ፈቃድ እና አላማህ ትክክል እንደሆነ ከተረዳህ ተራራዉ መንቀሳቀስ አለበት። በቃ ይሄዉ ነዉ። ወይም እግዚአብሔር አንድ የተሳሳተ ነገር ተናግሯል።

ለዚህም ነው እነዚህን ጉዳዮች በአብያተ ክርስቲያናት መድረክ ላይ ስጠቅስ ማንም ሰምቶ አያውቅም። ብቻቸውን ተውኳቸው። ተመልከቱ፣ ያ የእናንተ ጉዳይ ነው። በመለኮታዊ ስጦታ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ እንድታመጡ ልረዳችሁ በዚህ አለሁ። አየህ? ምንም ለውጥ አያመጣም የምታጠምቀው አንተ ነህ። ግን ከዚያ ሲመጣ....

34 በርግጥ ለሁሉም ነገር ተጠርቻለሁ። በቁጥር ለስንት ነገር እንደተጠራሁ አላዉቅም... ከ"ሥጋ ከተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ" እስከ "ዲያብሎስ" ድረስ። ልክ ነው - ለሁሉም ነገር። ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን፣ እኔ ወንድማችሁ ነኝ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ነኝ፣ ከሁላችሁ ጋር ለመንግሥቱ የምሠራ ነኝ፤ ያ እውነት ነው።

35 አሁን ቅር የማይላችሁ ከሆነ እና በቂ ጊዜ እንዳለን ካሰባችሁ እንዴት እንደተነጋገርን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ለአንድ ደቂቃ ቅር አይላችሁም አይደል ወንድሞች፣ ወንድም ኔስ እና እነርሱ? እንግዲህ እሺ ደህና፣ ጥቂት የሚረዳችሁ ሊሆን ይችላል። ነገሩን እንድትረዱት ሊጠቅማችሁ ይችላል.... ካስታወስኳቸው እና በዚያ ከነሳናቸዉ ነገሮች መካከል ጥቂቶቹን እዚህ ጻፍኩኝ እና .... ስለ ሥላሴ ያለኝን እምነት ጠየቁኝ። በእግዚአብሔር ሦስትነት ማመን አለማመኔን?

36 አሁን ወንድሞች ሆይ፣ ይህ ሲያልቅ፣ አብረን የነበርን ወንድማማቾች ሆነን እንደምንቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ። ለእናንተ ሸክም እንዳለኝ ይሰማኛል። ምክኒያቱም የእናንተ ሰዎች ወደ ስብሰባዬ መጥተዉ እዉነቱን ሳያዉቁ ወይም ተታለዉ እንዲመለሱ አልፈልግም። በመድረክ ከምሰብከዉ ዉጭ ጥያቄዎችን ለሚጽፉልኝ ሰዎች (በዚህ ፀሐፊዬ እና ሌሎችም አሉ) "ይህስ?" ወይም "ያኛዉስ?" ብለዉ ቢጠይቁኝ "ፓስተራችሁን ጠይቁ፣ ምክንያቱም እርሱ እስካሁን ከመራችሁ፣ መንፈስ ቅዱስን እስከትቀበሉ ድረስ ከመራችሁ ወደፊትም ይመራችኋል። ተመልከቱ፣ "ፓስተራችሁን ትጠይቃላችሁ"፣ ምክንያቱም እንደዚህ አይነት ትናንሽ ነገሮች ግራ መጋባት ስለሚፈጥሩ ተወዋለሁ።

37 "ብራንሃም ጸረ ድርጅት ነዉ" ይላሉ። አሁን እኔ ጸረ ድርጅት አይደለሁም! እኔ እንደማስበው ድርጅቶች ድንቅ ናቸው። ነገር ግን የድርጅቶች ስርዓት ከተበላሸ እኔ የምቃወመው ይህንን ነው። የፈለገ አይነት ዋንነስ ወይም ሦስትነት ወይም ምንም ቢሆን፣ አንድ የሆነ ቦታ ላይ ስትደርሱ ግን "ጉባዔ እግዚአብሔር ነን!" የምትል ሥርዓት።

"እሺ ከመንገዱ ማዶ ያለዉ ማነው?"

"ኧረ እነርሱም ወንድሞቻችን ናቸው። የተባበሩት ጴንጤዎች ይባላሉ።"

"ደህና፣ እዚያ ያለው ደግሞ ማነው?"

"ኦ፣ እነርሱም የፎርስኩዌር ወንድሞች ናቸው። ኧረ እኛ ድንቅ ወንድሞች ነን። እርስ በርሳችንም ታላቅ ኅብረት አለን።"

"እና ሁላችሁም አንድ አይነት ነገር ታምናላችሁ?"

"አዎ እናምናለን..."

"እናስ ታዲያ እንዲህ እንድትሆኑ ያደረጋችሁ ምንድነዉ?"

"እንግዲህ እነዚህ ወንድሞች በዚህ መንገድ ያጠምቃሉ፣ እነዚያ ደግሞ በዚያ መንገድ ያጠምቃሉ፣ እርስ በእርስ ይጋፈጣሉ። እነዚህም ያጠምቃሉ...."

38 ደቡብ አፍሪካ ያሉ ወንድሞች ጠየቁኝ። ... አንደኛው ቡድን በፊት ለፊታዉ አስተኝቶ ሦስት ጊዜ ያጠምቃል፣ ሌላኛው ደግሞ ወደ ኋላ ሦስት ጊዜ ያጠምቃል። "ከየት አመጣችሁት?" አልኩት።

ከእነርሱ አንዱ "መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በሞተ ጊዜ በፊቱ አዘነበለ" ይላል አለ።እናም "ሰዎችን በጥምቀት በግንባራቸዉ ወደፊት እናጠምቃለን" አለ።

እኔም "እሺ [ለሌላው ቡድን] አናንተስ?" አልኳቸዉ።

"አንድን ሰው ፊቱን ዝቅ አድርገህ ቀብረህ ታውቃለህ?" አሉ።

እንግዲህ በዚህ መልኩ ተለያይተው ሁለት ቡድን ወይም ሁለት ድርጅቶች ሆኑ። አቤት ምህረት ይብዛልን ወንድሞቼ። ዲያቢሎስ የሚፈልገው ይህንን ነው። እርሱ የሚፈልገው ይህንን ነው። ራሳችሁን ተቆጣጠሩ....

39 አሁን ተመልከቱ፣ ይህ የሐዋርያዊ እምነት ተልእኮ አይደለም፣ ወይም ደግሞ በሌላኛው በኩል ያለ የጴንጤቆስጤ ጉባኤ አይደለም። በፍፁም አይደለም። በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ ጥሩ ሰዎች አሉ። ልክ እዚህ እንዳሉት ማለት ነዉ።. ግን አያችሁ ነገሩ ስርአት ነው።

ልክ እንደ ካቶሊክ ነው፣ ደጋግሜ እንዳልኩት፣ ካቶሊክ ከሆነ እና ለድነት በክርስቶስ ላይ ቢደገፍ ድኗል። በእርግጠኝነት ትክክል ነው። በቤተ ክርስቲያን የሚደገፍ ከሆነ ጠፍቷል። እናንተ የጴንጤቆስጤ ወንድሞች ይህን እወቁ፣ ለድነት ወደ ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን የምንመለከት ከሆነ በጣም ሚስኪን ሰዎች መካከል ነን። ትክክል ነው፣ ምክንያቱም ጠፍተናል። እርግጥ ነው። ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የምንመለከት ከሆነ ግን ድነናል፣ ነገር ግን በተጠናቀቀው የመስቀል ላይ ሥራ በማመን ነው። እና እነዚህ ትንሽ የሚሰሩ ነገሮች እና ብራንዶች፣ ብዙ ለውጥ አያመጡም።

40 አሁን ለወንድም ስኪዝም እና ለወንድም ኔስ "ጥያቄዎቻችሁን ለመመለስ፣ ከሁለታችሁም ወገን አልሄድም። ሁለታችሁም ተሳስታችኋል፣ ተመልከቱ፣ ምክንያቱም በትምህርቴ ትክክል ሆኜ በልቤ ውስጥ ከመሳሳት ይልቅ በትምህርቴ ብሳሳት እና በልቤ ትክክል መሆንን መርጣለሁ።" "ዋናዉ ነገር የልብ ሁኔታ ነው" አልኳቸዉ።

ይህንን ለማወቅ ያንን ልምምድ አደረግሁ፡ አንድ ሰው ምንም ቢሰራ እናም የቱንም ያህል ልዩነት ቢኖረዉ እና ስለ እኔ የሚናገረው በልቤ ከሆነ - ከተግባር ብቻ ሳይሆን ከልቤ -ሌላዉን ሰዉ እንደምወድ ያንን ሰው ልወደዉ አልችልም፣ ከዚያ እዚህ ውስጥ የሆነ ስህተት እንዳለ አውቃለሁ፣ አያችሁ። ትክክል ነው። ምክንያቱም እሱ .... ምንም ቢሆን ....

41 አንድ ታናሽ ወንድም ከትንሽ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከጥቂት ጊዜ በፊት ወደዚህ መጣ፣እናም በዚያ ቆሞ "ይህ ሰው ሰይጣን ነው" አለ። ቀጥሎም "መንፈስ ቅዱስ አለ" ይላል አለ። "እንዲህ የሚባል ነገር የለም። መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ናቸዉ፣ እናም መለኮታዊ ፈውስ የተሰጠዉ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ነዉ" ለግማሽ ሰዓት ያህል ቀጠለ።

እኔም "ወንድሜ፣ አንድ አፍታ። በዚህ ጉዳይ ሃሳቤን እንድሰጥ እድል ልትሰጠኝ ያለብህ ይመስለኛል" አልኩት። አየህ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ በሚናገርበት ጉዳይ ተናገርከ፣ ዝም ባለበትም ዝም አልክ" አልኩት።

እርሱም፣ "ይሁን" አለ።

እኔም፣ "አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ተናግረሃል። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ በላይኛው ክፍል በወረደ ጊዜ ሴቶችን ጨምሮ 120 ሰዎች ነበሩ" ይላል። እናም ልትነግረኝ ትችላለህ? ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ የሌለው ይመስልሃል? ከበዓለ ሃምሳዉ ረጅም ጊዜ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል። "የፈውስ ስጦታ የተሰጠዉ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ነዉ" ብለሃል። እንግዲህ "እስጢፋኖስ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ አልነበረም። ሰባኪ አልነበረም። ዲያቆን ነበረ። ነገር ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ሰማርያ ወርዶ አጋንንት ያወጣ ነበር..." አልኩት። "አ ወንድም" እዚህ (ግልጽ ያልሆነ ቃል) በጣም ማድረግ ያለብዎት ጸጥ ማለት ነበር። በዚህ መልኩ ከተነጋገርን በኋላ "ሰይጣን ብለህ ስለሰደብከኝ ይቅር ብዬሃለሁ እንደዛ ለማለት እንዳልፈለክ ገብቶኛል" አልኩት። አዳምጦ ካበቃ በኋላ ቀረበኝና "አንድ ነገር መናገር ችላለሁ፣ አንተ የክርስቶስ መንፈስ አለህ።" እኔም እንዲህ አልኩት "አሁን ወንድሜ፣ እኔ የማን ነኝ? የሰይጣን? ወይስ የክርስቶስ?"

42 እኔ ግን እላችኋለሁ፣ አያችሁ፣ ይህ ሰው ምንም እንኳን ባይስማማም ወይም በብርቱ ቢቃወምም...እንደምወደው ሊናገር ይችላል።

በህይወቴ ሙሉ የዱር አራዊት አዳኝ ነኝ። ሰዎችም "እንዴት...?" ይላሉ። በዚያን ጊዜ በቢላ ኢጋዘን ላርድ ስል "አትፈራውም እንዴ?" አሉኝ።

እኔም፣ "አልፈራም። ብፈራው ኖሮ ይገድለኝ ነበር፣ አያችሁ"። ግን እዩ፣ እንስሶችን ማሳነስ አትችሉም። መፍራት አለመፍራታችሁን ያዉቃሉ። ፈረስ ትፈራላችሁ፣ ፈረሱ የሚያደርገውን ተመልከቱ። ይረግጣችኋል። ስለዚህ ከፈራችሁ ልትጋልቡት አትችሉም። ይህንን በደንብ ማወቅ አለባችሁ።

43 ሰይጣንም እንደዚሁ ነው። በሰዎች ዘንድም ተመመሳሳይ ነገር ነው። ሰዎችን መዉደድ አለባችሁ። ማስመሰል የለባችሁም። የእዉነት ልንወድ ይገባል፣ አለበለዚያ ቀለማችን ወይም እዉነተኛ መልካችን የሆነ ቦታ መገለጡ አይቀርም፣አያችሁ። ትክክል ነው። ሰዎችን የእውነት መውደድ አለባችሁ፣ እነርሱም እንደምትወዷቸው ያውቃሉ። አያችሁ፣ የሆነ ነገር አለ።

እናም ሰውዬው ከጥቂት ቀናት በፊት ለባለቤቴ ደዉሎ፣ "ወንድም ብራንሃም አለ?" ብሎ ጠየቃት።

"የለም" አለችዉ። "እሺ፣ አንድ ነገር ማለት አለብኝ፣ በነገረ መለኮት ከእርሱ ጋር አልተስማማሁም፣ ግን የክርስቶስ አገልጋይ ነዉ" አላት።

እናም ከዚያ ከመውጣቴ በፊት እንዲህ የሚል ደብዳቤ ላከልኝ "ልክ እንደተመለስክ መጣለሁ። የምትናገረውን ያንን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ፈልገዋለሁ።"

44 ስለዚህ አያችሁ...መጥፎ ስሜት ቢኖረኝ ኖሮ ማለትም "ለአንተ ምንም ነገር የለም። የድሮ ቤተ እምነትህ ጥሩ አይደለም፣ ሁላችሁም የክርስቶስ ቤተ ክርስትያን ሰዎች ጥሩ አይደላችሁም። አንተ ጥሩ አይደለህም፣ ሰይጣኖች ናችሁ" ብዬ ቢሆን ኖሮ ያንን ሰው በፍፁም አላሸንፍም ነበር። እንደምወደው ነግሬዉ ነገር ግን ከልቤ ባይሆን ኖሮ እርሱ የበለጠ ያውቃል። በዚህ ጉዳይ ያለዉ እዉነታ ይሄ ነዉ። ከልብህ መሆን አለበት።

በነዚያ ምሽቶች በዚህ ማስተዋል ስር ሆኜ መድረክ ላይ ስወጣ፣ አያችሁ። ስለሱ አላስብም፣ እራት አልበላም፣ በጾም እና ጸሎት ክፍሉ ውስጥ እቆያለሁ። ምክንያቱም እርሱ እንደሚያደርገው ቃል ገብቶልኛል። እናም ስለዚህ እኔ ያለምንም ጥርጥር ሄዳለሁ፣ ምክንያቱም እርሱ እንደሚያደርገው ቃል ገብቶልኛል። ስለዚህ አያችሁ፣ የልብ መሻቴ ምን እንደሆነ አውቃለሁ። አላማዬ ምንድነዉ?—የእግዚአብሔርን መንግስት ማስፋት ነዉ።

አንድ ሰው በዚህ ወይም በዚያ መንገድ ቢሄድ፣ የፈለገዉ ቤተ ክርስቲያን ቢሄድ፣ ወደ ክርስቶስ እስከመጣ ድረስ፣ ለእኔ ምንም አይደለም። እናም ያ በልቤ ውስጥ ነው፣ አያችሁ። ሄደን ወደ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብንቀላቀል ምንም ችግር የለውም፣ ያ ጥሩ ነው። የትኛውንም ቤተ ክርስቲያን ቢቀላቀል ለኔ ምንም አይደለም። ነገር ግን ... ነፍሱ በክርስቶስ እንድትሆን ፈልጋሁ። ዋናው ነገር ይሄ ነው።

45 እናም "ወንድም ኔስ፣ ላለመለያየት....ቅር የማይልህ ከሆነ አሁን እየሄድኩ ነው...." አልኩት። ነገር ግን "ከመሄዴ በፊት ይህን መናገር እና ማብራራት እፈልጋለሁ..." አልኩት። እናም ወንድሞቼ ፈቃደኛ ከሆናችሁ ሄዳችሁ ይህንን ጉዳይ ለጉባዔያችሁ ባትነግሩ ደስ ይለኛል። ዉለታ ዋሉልኝ፣ በቃ ወንድማችሁ ልሁን። ከተሳሳትኩ ይቅርበሉኝ። ነገር ግን አንድ ነገር ልገልጥላችሁ ወዳለሁ፣ ዛሬ ማለዳ ሁለቱ ቡድኖች ማለትም ዋንነስ (ONESS) እና ሥላሴ አማኞች ጉባዔ እግዚአብሔር በዚህ ተቀምጠዋል።

እናም አሁን ይህን መናገር ፈልጋለሁ። ሁለቱም ወገኖች አንዱ ከሌላው ጋር እስከተከራከሩ ድረስ የተሳሳቱ ናቸው ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም የልባቸዉ መሻት የተሳሳተ ነው። እናም የልብህ መሻት የተሳሳተ እስከሆነ ድረስ አላማህ ምንም ይሁን ምን በጭራሽ አይሰራም። እዉነታዉ ይሄ ነው።

46 አንዳንድ ሰዎች "ወንድም ብራንሃም፣ አንተ ኢየሱስ ብቻ (Jesus Only) ነህ" ይላሉ።

ይህ ስህተት ነው። እኔ ዋንነስ ወይም ኢየሱስ ብቻ አይደለሁም።

ሌሎች ደግሞ፣ "ወንድም ብራንሃም፣ አንተ የሥላሴ እምነት ተከታይ ነህ?" ብለዉ ይጠይቃሉ።

በፍፁም የሥላሴ እምነት ተከታይ አይደለሁም። እኔ ክርስቲያን ነኝ። "ሥላሴያዉያን" የሚለው ቃል... መጽሐፍ ቅዱስ "ሥላሴ" የሚለዉን ቃል አያነሳም። ሦስት የተለያዩ አካላት ወይም ማንነት ያላቸዉ አማልክቶች አሉ ብዬ አላምንም። በሦስት ቢሮዎች የተገለጠ አንድ አምላክ እንዳለ አምናለሁ። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ። ለዚህም ነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድናጠምቅ የተላክነዉ። ከሰማየ ሰማያት ዝቅ ብሎ የሚወርድ እግዚአብሔር (God condescending) እንደሆነ አምናለሁ።

47 እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለሰው በተገለጠ ጊዜ በእሳት ዓምድ አምሳል ነበረ የተገለጠዉ። ያንን ታምናላችሁ አይደል? የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ.... በምድረ በዳ የነበረው የእሳት ዓምድ ሎጎስ መሆኑን ያውቃል። ያ የቃል ኪዳኑ መልአክ ነው፣ እርሱም ክርስቶስ ነው። በቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 6፣ "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" ይላል። እርሱ እርሱ ነዉ። ስለዚህም እርሱ እግዚአብሔር ነበረ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ነበረ። አንድ ሰው ተራራውን ቢነካው መገደል አለበት። አያችሁ፣ በጣም ጥሩ።

48 አሁን፣ ያ እግዚአብሔር ራሱ በፈጠረው ፍጥረት ውስጥ ራሱን ለመስራት እየሞከረ ነበር። ነገር ግን ኃጢአተኞች ስለነበሩ ወደ እነርሱ ሊቀርብ አልቻለም፣ የፍየሎች እና የበጎች ደም ኃጢአትን ፈጽሞ አላስወገደም። ያንን እናውቃለን። ኃጢአትን ብቻ ሸፍኗል።

አሁን ግን ያ የእሳት ዓምድ የሆነው አምላክ በልጁ በኩል ሥጋ ሆነ እናም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚባል አካል አደረ። መጽሐፍ ቅዱስ “በእርሱ የመለኮት ሙላት በሰውነት ተገልጦ ይኖራል” ይላል። ኢየሱስም እንዲህ አለ...መልካም፣ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16፣ “እግዚአብሔርንም የመምሰልሚስጥር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤ [ታላቅ ብለው ሊጠሩት ከቻሉ፣ ለምን? ምን እናድርግ? አያችሁ?] እግዚአብሔርንም የመምሰል ሚስጥር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የጸደቀ፥ ለመላእክት የታየ፥በአሕዛብ የተሰበከ፥ በዓለም የታመነ፥ በክብር ያረገ።” ወዘተ።

49 እናም አሁን፣ በቅዱስ ዮሐንስ 14 ላይ ለቶማስ፣ “እኔን ባየህ ጊዜ አብን አይተሃል። 'ለምንስ አብን አሳየን' ትላለህ?” መጽሐፍ ቅዱስ “እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር” ይላል። አሁን ተመልከቱ።

እግዚአብሔር ሦስት ሰዎች ሊሆን አይችልም። ሦስት አማልክት ሊሆን አይችልም። ኢየሱስም በአንድ ጊዜ የራሱ አባት ሊሆን አይችልም፤ ተመልከቱ። ስለዚህ አያችሁ፣ ይሄ ሁለቱንም ፍፁም ስህተት ያደርጋቸዋል።

እናም አሁን ልብ ካላችሁ ፈፅሞ ቦታ የለም....ሦስት አማልክቶች ካሉን አሕዛብ ነን። አሁን ያንን እናውቃለን። በአንድ ወቅት ከአንድ አይሁዳዊ ጋር ስነጋገር “ከመካከላቸው አምላክህ የትኛው ነው? አምላክህ የትኛው ነው? አብ፣ ወልድ፣ ወይስ መንፈስ ቅዱስ፣ ያንተ የትኛው ነው?” አለኝ።

እኔም “ሦስት አማልክት የሉም” አልኩት

እርሱም፡- “እግዚአብሔርን ሦስት ቦታ ቆራርጠህ ለአንድ አይሁዳዊ ልትሰጠው አትችልም” አለኝ።

“በፍፁም ክቡርነቶ” አልኩት። ታውቃላችሁ.....ጀን ሪያን በኤፍ ቲ. ዌይን ከዓይነ ስውርነት ሲፈወስ ይህ ረቢ በዚህ ቤንተን ወደብ፣ “እግዚአብሔርን ሦስት ቦታ ቆራርጠህ ለአንድ አይሁዳዊ ልትሰጠው አትችልም” አለኝ።

“በፍፁም ክቡርነቶ” አልኩት። እኔም፣ “ረቢ፣ ነቢያትን ታምናለህ?” አልኩት።

እሱም “አዎን” አለኝ።

50 እኔም፣ “በኢሳይያስ 9፡6 ላይ ስለ ማን ነው የሚናገረው? ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃዉ ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።” አልኩት።

እርሱም “መሲሑ ነበር” አለኝ።

እኔም፣ “ታዲያ፣ መምህር ሆይ፣ መሲሑ ከእግዚአብሔር ጋር ምን ዝምድና ይኖረዋል?” አልኩት።

እርሱም “እርሱ እግዚአብሔር ይሆናል” አለኝ።

እኔም “ያሰብኩት ያንን ነው። አየህ፥ ያ በትክክል ልክ ነው። ያ እርሱ የሆነዉ ነው።” እናም፣ “ኢየሱስ ነቢዩ እንደሚያደርገው የተናገረውን በትክክል ሳይፈጽም የቀረውን አሁን ንገረኝ” አልኩት። ማልቀስ ጀመረ እናም ወደ ዉጭ ወጣ።

እኔም፣ “በዚህ፣ ጀን ራያን የአይኑን ብርሃን አገኘ” አልኩት።

እርሱም፡- “ልጅ ያለው እግዚአብሔር ይራቅ” አለ

እኔም እንዲህ አልኩት፣ “ታላቁ ይሖዋ ነቢዩ እንደሚለው አንዲት ሴትን ፀለላት፣ እናም የደም ሕዋስ ፈጠረ፣ እናም በዚያ የደም ሴል በኩል የክርስቶስ አካል መጣ።

51 ተመልከት ረቢ፣ “በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው መስዋዕት ሊሰዋ ሲሄድ ጠቦት ይዞ ይሄዳል። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንደጣሰ አውቆ ለሃጢአቱ መስዋዕት ያቀርባል። ኃጢአቱን ይናዘዛል ጠቦቱም ይታረዳል። እጆቹ በበጉ ጠቦት ላይ እንዳሉ፣ ለኃጢአቱ መሞት የነበረበት እርሱ ራሱ መሆኑን አዉቆ ነገር ግን በእርሱ ፈንታ በጉ እንዲተካ ይናዘዛል። በጉን ያርዳል። እናም የደም ህዋሱን ይቆርጣል። የበጉ ሕይወት እስከትወጣ ድረስ በእጁ በጉን ይይዛል። ከዚያም ካህኑ የጠቦቱን ደም በእሳት ላይ ይጥላል። ይህም የናሱ የፍርድ መሠዊያ ነው።

“ከዚያም” አልኩት፣ “ያ ሰውዬ፣ በጉ የእርሱን ሃጢያት እንደ ወሰደ አዉቆ ከዚያ ይወጣል። ነገር ግን ሲገባ የነበረዉን የልብ ምኞት ሲወጣም ይዞት ይወጣል። ምክኒያቱም የጠቦቱ ደም የሰዉዬዉን ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ሊያስወግድ አልቻለም። ነገር ግን አምላኪው ሰዉ አንድ ጊዜ በዚህ መልኩ መስዋዕቱን ከፈፀመ በኋላ የኃጢአት ሕሊና አይኖረዉም። በዚያም በየዓመቱ የሚቀርብ መስዋዕት ነበር። እንግዲህ አምላኪው ሰዉ አንድ ጊዜ በዚህ ሁኔታ መስዋእቱን ካቀረበ በኋላ ዳግም የኃጢአት ሕሊና አይኖረዉም። ምክንያቱም፣ እነሆ፣ ረቢ፣ ከወንድ ጾታ ወደ ሴት የምትመጣዉ በሂሞግሎቢን የደም ሴል ውስጥ የምትጀምረው ትንሽ ህይወት እንቁላል ትሰራለች። ዶሮ እንቁላል ልትጥል ትችላለች። ነገር ግን ከወንዱ ወፍ ጋር ካልተዳቀለ በጭራሽ አትፈለፍልም።.

52 እኔም፣ “ከዚያም ጊዜንና ቦታን ሁሉ የሞላው ታላቁ እግዚአብሔር፣ እስከ አንዲት ትንሽ ጀርም እስከ ሴት ማኅፀን ድረስ ወረደ።” ከዛም እንዲህ አልኩት፡- “ዛሬ ስንድን.... ኢየሱስ አይሁዳዊ ወይም አህዛብ አልነበረም፣ ምክንያቱም እንቁላል ሥጋን ብቻ ያበቅላል። ደሙ ሕይወት ነበረው፣ አያችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ”ድነት ያገኘነዉ በእግዚአብሔር ደም ነዉ“ ይላል። አያችሁ፤ አይሁዳዊ ወይም አሕዛብ አልነበረም፤ እርሱ እግዚአብሔር ነበር። ስለዚህ ወደ መሠዊያው ስንመጣ እና እጃችንን በእምነት በራሱ ላይ ጭነን እና በቀራንዮ የነበረዉን እንባ እና ስቃይ ሲሰማን እና እንደተሳሳትን ኃጢአታችንን ስንናዘዝ - እናም በእኛ ምትክ እርሱ እንደሞተ.... ስናምን ድነት ይሆናል።

ከዚያም “አየህ” አልኩት። የፈሰሰዉ የዚያ ጠቦት በግ ደም በዚህ ላይ ተመልሶ ሊመጣ አልቻለም...የተቆረጠዉ ሴል ደም፣ የበጉ የደም ሴል በመቆረጡ ምክኒያት የወጣዉ የበጉ ህይወት ተመልሶ ወደ አምላኪዉ ሰዉ ሊገባ አልቻለም። ምክንያቱም የእንስሳት ህይወት ነበር። እናም ከሰው ህይወት ጋር አይጣጣምም።

53 “አሁን በዚህ ጊዜ ግን፣ የደም ሴሉ ሲቆረጥ፣ ሰው ብቻ አልነበረም። የፈሰሰዉ ወይም የወጣዉ ወይም የተለቀቀው የእግዚአብሔር ሕይወት

ነበር። እናም አምላኪው ሰዉ በእግዚአብሔር ልጅ ራስ (ልክ እንደ በጉ) ላይ በእምነት እጁን ጭኖ እና ኃጢአቱን ሲናዘዝ የሌላ እንሰሳ ወይም የሌላ ሰው ህይወት ሳይሆን የራሱ የእግዚአብሔር ሕይወት ወደዚህ ሰው ተመልሶ ይመጣል- እርሱም የዘላለም ሕይወት ነው። 'ዞዊ' የሚለው ቃል ሲተረጎም፣ 'የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት' ማለት ነዉ። እግዚአብሔር ዞዊ ወይም የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጠን ተናግሯል። እናም አሁን እኛ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች ነን። አለህ።”

እኔም “አሁን ነገሩ ምንድን ነው? ከሰማየ ሰማያት የሚወርድ አምላክ ነው።” አልኩት።

እንግዲህ ወደ ሰዉ መጣ...በመጀመሪያ ማንም ሊነካው አልቻም ነበር። ምክንያቱም ሰው ኃጢአት ሠርቷል። ከዚያም...ኃጢአትን ሊቀምስ ኃጢአትንም ሊያስወግድ በሥጋ ወረደ። አየህ፣ እግዚአብሔር ፍፁም ጻድቅ ለመሆን የሚያደርገው ብቸኛው ነገር በዚያ መንገድ ማድረግ ብቻ ነው።

54 ለምሳሌ ያህል እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ስልጣን እንዳለው ሁሉ እኔም ዛሬ ማለዳ በዚህ ጉባዔ ላይ ሥልጣን ቢኖረኝ እና “ግርግዳ ላይ የተለጠፈዉን ፖስት የሚያይ የመጀመሪያው ሰው ይሞታል” ብል እናም ቶሚ ሂክስ ፖስቱን ቢያየዉ? እናም አሁን፣ ለምሳሌ፣ “ወንድም ካርልሰን፣ ለቶሚ ሂክስ ትሞታለህ” ብለዉ፣ ያ ፍትሃዊ አይሆንም። ወይም ደግሞ “ሊዮ፣ አንቺ ፀሀፊዬ ነሽ። ለቶሚ ሂክስ ትሞቻለሽ።” ብል ያ ፍትሃዊ አይሆንም። “ቢሊ ፖል ልጄ ሆይ አንተ ለእርሱ ትሞታለህ” ያ ፍትሃዊ አይደለም። እኔ ፍትሃዊ ልሆን የምችልበት ብቸኛው መንገድ እኔ ራሴ የቶሚ ሂክስን ቦታ መተካት ነዉ።እናም እግዚአብሔር ያደረገው ይህንኑ ነው።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ እናም ፈጠረ....ራሱን ለወጠ። ሰዎች ስለ “ትንሹ ይሖዋ” ሲያስቡ ይደነቃሉ። ጎልማሳ ሰው ሆኖ መምጣት ይችል ነበር፣ ነገር ግን በፋንድያ ክምር በግርግም ተወለደ። ትንሹ ይሖዋ እንደ ሕፃን አለቀሰ! ትንሹ ይሖዋ እንደ ልጅ ተጫወተ! ትንሹ ይሖዋ እንደ ሠራተኛ አናጢ ሆነ! በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ያለ ትንሹ ይሖዋ! ይሖዋ በሰማያትና በምድር መካከል ተንጠልጥሎ ሰካራሞች እና ወታደሮች ፊቱ ላይ ተፉበት! ይሖዋ ለልጆቹ ሞተ! ይሖዋ ለመቤዠት ሞተ! ሌላ ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነው! እነሆ፥ እግዚአብሔር... ያ አገልግሎቱ ወይም ሥራው ነበረ። ለምን? ወደ ሰው ልብ ለመመለስ እየሞከረ ነበር።

55 አሁን፣ በዚያ ልንነካው አልቻልንም። እዚህ ድግሞ በእጃችን ዳሰስነዉ። እንግዲህ ያንን ሥጋ መስዋዕት በማቅረብ ምን አደረገ? በውስጣችን ይሖዋ ይሆናል። እኛ የእርሱ አካሎች ወይም ክፍሎች ነን።

በበዓለ ሃምሳ ቀን የእሳቱ ዓምድ ራሱን በሃይል ገለጠ፣ እናም የተከፋፈሉ የእሳት ልሳኖች በዚያ በነበሩ በእያንዳንዳቸው ሰዎች ላይ ተቀመጡ፣ ይህም እግዚአብሔር በራሱ ቤተ ክርስቲያን መካከል ራሱን እንደከፋፈለ ያሳያል። እንግዲያውስ ወንድሞች ሆይ፣ መሰባሰብ ከቻልን ብቻ ነዉ ያንን የእግዚአብሔር ሙላተ አንድነት መገናኘት የምንችለዉ! ከዚያም አንድ ላይ ስንሰበሰብ ይሖዋን በሙላት እናገኘዋለን። ግን እንዴት፣ ይሄኛዉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ ልሳን ሲናገር ሌላኛዉ ደግሞ....አንዱ በአንድ ቦታ የእሳት ፍንጣሪ ይዞ ብቻዉን ሲቀመጥ.... ይሄኛዉ ደግሞ....ይሄንን ክብር አንድ ላይ እናድርገው።

56 እግዚአብሔር በበዓለ ሃምሳ ቀን በወረደ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ “በእያንዳንዳቸው ላይ የእሳት ልሳኖች ተቀመጡባቸዉ” ይለናል እነርሱም.... እንደ እሳት ያሉ ልሳኖች። ያ የእሳት ዓምድ ነበር እኛ ወንድማማች እንሆን ዘንድ ራሱን በሕዝብ መካከል ከፋፍሎ የወረደዉ። “እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ። እኔ በእናንተ እናንተም በእኔ” እና እኛ አንድ ነን! አንድ ነን - አልተከፋፈልንም!

57 አሁን ይሖዋ አምላክ እዚህ ላይ በራሱ የቅድስና ሕግ ምክኒያት የሰውን ዘር መንካት አልቻለም። ይሖዋ አምላክ ለእኛ ሲል ኃጢአት ሆነ። እናም ራሱ ይሖዋ አምላክ የኃጢአትን ዋጋ ከፍሎ በእኛ ውስጥ ሊኖር መጣ። እግዚአብሔር ከእኛ በላይ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፣እግዚአብሔር በእኛ ዉስጥ። ሦስት አማልክት አይደሉም - አንድ አምላክ።

ፕሮፌሰሮች ይህን ለማወቅ እየሞከሩ ያብዳሉ። ነገሩ መገለጥ ነው! ለአንተ መገለጥ አለበት። አሁን ወደ ጥምቀት ጉዳይ ስንመጣ፣ ብዙ ሰዎች... “

አሁን፣ ወንድሞች ሆይ፣ ራሳችሁ ማጥመቅ አለባችሁ ወይም....“ ለወንድም ስክዝም እና ለወንድም ኔስ እንዳልኳቸው ነው። በዚህ ዙርያ ክርክር አለ፣ ብዙዎቻችሁ በዚህ ያላችሁ ምሁራን ከእኔ ትሻላላችሁ። በራሴ በኩል ግን በጉዳዩ ላይ ብዙ ጥናት አድርጌያለሁ። የቅድመ ኒቂያ ጉባዔ አባቶችን ታሪክ እና የኒቂያ ካውንስልን እንዲሁም ሌሎች መሰል ታሪኮችን አንብቤአለሁ። አጀንዳዉ የተነሳዉ በኒቂያ ጉባዔ ነዉ። ሁለቱም ወገኖች ወደ ዘር ሄዱ - የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሥላሴን ጽንፍ ስትይዝ ፣ ሌላኛው ደግሞ ወደ አንድነት(Unitarian)- እናም ሁለቱም ወገኖች በዚህ ተለያዩ።

በትክክል የሆነዉ ይሄ ነዉ፣ ምክንያቱም ጉዳዩ የሰው እጅ ነበረበት! እግዚአብሔር እንዲሰራ መፍቀድ አለብህ። እኛ ነገሩን ለማስተካከል መሞከር አይጠበቅብንም። ወንድማማቾች እንሁን። በቃ እኛ ወደፊት እንቀጥል እና እግዚአብሔር ደግሞ ሊያደርግ የፈለገዉን እንዲያደርግእንፍቀድ። እሱ ወሰን የሌለው እና ሁሉንም ነገር የሚያውቅ ከሆነ እናም ደግሞ መጨረሻውን ከመጀመሪያው የሚያዉቅ ከሆነ እንዴት እኛ ማንኛዉንም ነገር ማድረግ እንችላለን? ዝም ብለህ ወደፊት ቀጥል። መንገዱ እንደዛ ነው...ትናንት ማምሻ በታላቁ ኢያሱ ዙርያ እንደተናገርኩት መራመድህን ወደፊት ቀጥል።

58 አሁን ተመልከት፣ ሶስት አማልክት ካሉ....አሁን ይህ ምን ያህል አስቂኝ እንደሆነ ላሳይህ ፈልጋለሁ። ሦስት አማልክት ካሉ፣ እንግዲያውስ ኢየሱስ የራሱ አባት ነበር... ወይም ኢየሱስ አንድ ሆኖ ሳለ የራሱ አባት ሊሆን አይችልም። ሦስት ከሆኑ ደግሞ ከድንግል አልተወለደም። አሁን ስንት...ናቸዉ?

እኔ ይህ እግዚአብሔር አብ ነው፣ ይህ እግዚአብሔር ወልድ ነው፣ ይህ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው እላለሁ። አሁን በዚህ ላላችሁ የተለያዩ ወንድሞች፣ ይህንን ለአንድ ደቂቃ ብቻ ተመልከቱ፣ ለመጠቆም የሞከርኩትን ታያላችሁ። እግዚአብሔር ነገሩን እንዲያሳያችሁ ጸልያለሁ። አሁን ተመልከቱ፣ እናንተ ሁለታችሁም አንድ አይነት ነገር ታምናላችሁ፣ ነገር ግን ዲያቢሎስ በመካከላችሁ ገብቶ በዚህ ጉዳይ ለያያችሁ። በትክክልም ተመሳሳይ ነገር ነው፣ እናም በእግዚአብሄር እርዳታ እና በእግዚአብሐር መጽሐፍ ቅዱስ አረጋግጥላችኋለሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ካልሆነ አትቀበሉት። ትክክል ነው።

59 አሁን ግን ተመልከቱ፣ ይህ ምንድን ነው? እግዚአብሐር አብ፤ ይህ እግዚአብሔር ወልድ ነው፥ ይህ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። ደህና፣

*አሁን እስቲ ለአንድ ደቂቃ ብቻ ቆም እንበል—ሦስቱን እዚያ ላይ አስቀምጠን፡ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ።*

*(ኧረ ይህን ለማድረግ ጊዜ አይኖረኝም። እሺ፣ በተቻለኝ መጠን ለመፍጠን ሞክራለሁ፣ ወንድሞቼ ሆይ ይቅር በሉኝ፣ ከእናንተ ጋር መነጋገር አልነበረብኝም እናም ግን አሁን ልንገራችሁ።)*

60 *እናም አሁን ተመልከቱ፥ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ። እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ማን ነበር? እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነበር። ሁላችንም ይህን እናምናለን። ይህ ግን ትክክል ነው? እሺ ደህና። እንግዲህ፣ ማቴዎስ 28፡19ን ስንወስድ፣ ኢየሱስ፡- "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸዉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸዉ፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜከእናንተ ጋር ነኝ።" ከአሥር ቀን በኋላ ጴጥሮስ፡- "ንስሐ ግቡ፥ እናም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።" የሆነ ቦታ ቀጥተኛ የሆነ ተቃርኖ አለ።*

*አሁን እንዲህ አናድርግ… እያንዳንዱ መስኪሯል እና ነገሮችን። እነሆ። ነገሩ ይሄ ነዉ። እምነቴ ይኸውና። እነሆ በፊታችሁ አስቀምጫለው ወንድሞቼ። በመድረክ ላይ ይህን አልናገርም። የእናንተ ጉዳይ ነው፣ ነገር ግን በሁለቱም በኩል የማየውን ላሳያችሁ እፈልጋለሁ፣ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ይገልጥላችኋል፣ ተመልከቱ።*

61 *አሁን፣ ማቴዎስ 28፡19.... እናም ማቴዎስ 28፡19 ከሐዋርያት ስራ 2፡38 ጋር የሚቃረን ከሆነ እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ ይጋጫል ልንል ነዉ፣ እናም በወረቀቱ የተጻፈዉ ዋጋ አይኖረዉም ማለትነዉ። አሁን በማቴዎስ አስራ ስድስተኛው ምዕራፍ ላይ ያለዉን ካስተዋላችሁ፣ ኢየሱስ ለጴጥሮስ መገለጥ እና ቁልፎች ሰጠው።*

*አሁን፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአንዳንድ ሰው ሰራሽ ሥነ-መለኮት ዘዴዎች እንዳልተገለጸ አስታውሱ። አይደለም። መገለጥ ነው።*

*ሲጀመር ነገሩ በመገለጥ ነበር። አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ለምን አቀረበ? ኮክ፣ ፖም፣ ብርቱካን እንዳልሆነ ተገለጠለት። ፖም ሴቶች ራቁታቸውን መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ካደረጋቸው፣ ወንድሜ እንደገና ፖም ብናቀብላቸዉ ይሻለናል። አይመስላችሁም? ይህ ሃይማኖታዊ መስዋዕት ይመስላል፣ ግን ይህን ለማለት ፈልጌ አይደለም። ነገሩ ፖም አልነበረም። በፍጹም ከቡርነቶ። እንግዲህ ያ ከሆነ ደግሞ ለአቤል የአባቱ ደም እንደሆነ ተገለጠለት ስለዚህም መገለጥ ነውና ደም አቀረበ። ነገሩ ሁሉ የተገነባው በዚያ ላይ ነው።*

62 *አሁን እነሆ አንድ ያልተማረ ሽማግሌ ዓሣ አጥማጅ አለ። በቂ ትምህርት አልነበረዉም።... መጽሐፍ ቅዱስ "ያልተማረ መሃይም ነው" ይላል። እርሱ ግን በዚያ ቆሞ ነበር፣ እናም ኢየሱስ፣ "የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ትላላችሁ?" ሲል ጠየቀ።*

*አንዱ፣ "አንተ ሙሴ ነህ—እነርሱ ሙሴ ነዉ ይሉሃል" አለ።*

*ሌላኛዉ ደግሞ፣ "አንተ ኤርምያስ ወይም ከሌሎች ነቢያት አንዱ ነህ ይላሉ" አለ።*

*ኢየሱስም፣ "ጥያቄው እሱ አይደለም። እናንተ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?" አላቸዉ።*

*ጴጥሮስም ወዲያው "አንተ የሕያዉ እግዚአብሔር ልጅ ነህ" አለዉ።*

*እርሱም፡- "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ብፁዕ ነህ (አሁን ተመልከቱ)። በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም።" አለዉ።*

63 *አሁን ተመልከቱ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የገነባዉ በጴጥሮስ ላይ ነዉ" ብላ ትናገራለች። ያ ስህተት ነው። የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የገነባዉ በራሱ ላይ ነዉ" ትላለች። እንግዲህ አሁን በደንብ አስተዉሉ እና እዉነቱ የት እንዳለ እወቁ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የገነባዉ በራሱ ማንነት (ማን እንደሆነ በመረዳት) መንፈሳዊመገላጥ ላይ ነዉ። ምክኒያቱም "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ብፁዕ ነህ። በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም። እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ (የምን ዓለት - መገለጥ)ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።" አለዉ።*

*ከዚያ በኋላ ጴጥሮስ ማቴዎስ 28 ሲጠቀስ በቦታው ቆሞ ዘወር ብሎ ከአሥር ቀን በኋላ ያን መገለጥ ይዞ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲያጠምቅ.... ለምን በዚህ ስም አጠመቀ? የእግዚአብሔር መገለጥ እና የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ቁልፎች ነበሩት፣ ወንድም።*

64 *አሁን፣ አንዳችሁን ወገን ለደቂቃ ያህል ልጎዳችሁ እችላለሁ። ግን አንድ ደቂቃ ብቻ ታገሱኝ።በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ሰዉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የዉሃ ጥምቀት የተጠመቀበት አንድም ቦታ የለም። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አንድም ቦታ የለም። ካለ ደግሞ አሳዩኝ። ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እስከተመሰረተችበት ጊዜ ድረስ በተቀደሰው ታሪክ ውስጥ የትኛውም ቦታ ማግኘት ከቻላችሁ፣ እንድታሳዩኝ እፈልጋለሁ። የትም ቦታ የለም፣ እናም ያ እውነት ነው። አሁን ግን አንድ ደቂቃ ጠብቁኝ - እናንተ ዋንነስ (Oneness/Jesus Only) አንድ ሰከንድ ታገሱኝ። አሁን፣ የትም ቦታ ይሄ የለም... ማንም ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዉሃ ጥምቀት ሥነ ሥርዓት - በአብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ - ስም መደረጉን የሚያሳይ ጥቅስ ካለ መጥታችሁ መዚህ መልኩ ማን እንደተጠመቀ ልትነግሩኝ ይገባል።*

65 *ከእነርሱም አንዳንዶቹ፡— "ኢየሱስ የተናገረውን እወስዳለሁ እንጂ ጴጥሮስ የተናገረውን አይደለም" ይላሉ። እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ከሆኑ እኛ ምን እናደርጋለን? ሁሉም ነገር የአምላክ ካልሆነ ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የትኛው ነው? ሁሉም ነገር መገጣጠም እና እርስ በእርሱ መናበብ አለበት። እናም የእግዚአብሔር መገለጥ ብቻ...ትምህርት ቤቶቻችን ይህንን ፈጽሞ አያስተምሩትም። ልታዩት የሚገባ መገለጥ ነዉ።*

*ከዚያም ሁለቱ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ከሆኑ ምን ዓይነት መጽሐፍ ቅዱስ እያነበብን ነው? የዮሐንስ ወንጌል 14 ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዴት አውቃለሁ? የዮሐንስ ወንጌል 3 ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዴት አውቃለሁ? እንዴት አውቃለሁ፣ አያችሁ? ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዲኖረኝ ማድረግ የሚችል ብቸኛው መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል መሆኑን ማወቅ እና ትክክል እንደሆነ ማመን እንዲሁም ራሴን በትክክሉ የመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ መምራት ነዉ። ምንም እንኳን ባይገባኝም እቀበለዋለሁ። ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት እርስ በእርስ የሚቃረኑ ነጥቦች ሲያጋጥሙ ያን ጊዜ መልሱን ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርባለሁ። እናም በሌሊት ስብሰባችን ያገኘኝ ያው ራሱ መልአክ ይህን ደግሞ አስተማረኝ።*

66 አሁን ፣ ይህ እንዴት እንደሆነ ተመልከቱ። አሁን፣ የማቴዎስ ወንጌል 28፡19ን እስቲ ለአንድ አፍታ ብቻ እንመልከት። አሁን ደግሞ እዚህ ጋር የሐዋርያት ሥራ 2፡38ን እወስዳለሁ፣ ጴጥሮስ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ" ብሎ የተናገረውን ነው። ማቴዎስም "አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ" ብሏል። አሁን አዳምጡ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "በአብ ስም፣ በወልድ ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" አላለም። በፍፁም እንደዛ አላለም። ስም፣ ስም፣ እና ስም የለም። "በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስሞች አጥምቋቸው" በፍፁም አላለም። ምክንያቱም ትርጉም አይሰጥም።

እርሱ ያለዉ "በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም [ስ-ም] አጥምቃቸው።" ነዉ። ትክክል ነው? የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ (እና፣ እና፣ እና የሚሉ አያያዦች ስሞች አይደሉም)። በአብ ስም፣ በወልድ ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም። በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስሞች አይደለም። ነገር ግን በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም (ስ-ም፣ ነጠላ) ነዉ።

አሁን ለማጥመቅ ከመካከላቸው ትክክለኛው ስም የትኛው ነው? አንድ ስም ነው። የትኛው ነው? አባት ትክክለኛው ስም ነው? ወይስ ወልድ ትክክለኛው ስም ነው? ወይስ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛ ስም ነው? የሆነ ቦታ አንድ ስም ነዉ። ያ ትክክል ነው?

67 ደህና እንግዲህ፣ አሁን አንድ የሆነ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ነገሩ ስም ከሆነ .... ታዲያ ኢየሱስ "በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" ካለ.... ስንቶች ይህንን ኢየሱስ እንደተናገረ ያምናሉ? በማቴዎስ 28፡19 የተፃፈ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነዉ። በአብ በወልድ ስም .... [ወንድም ብራንሃም በጎንዮሽ ለአንድ ሰው ተናገረ]

68 አሁን በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም .... አሁን አድምጡ ወንድሞች። የአብ ስም የሚባል ነገር የለም። ምክንያቱም አብ ስም አይደለም። ማዕረግ ወይም ሃላፊነት ነው። የወልድ ስም የሚባል ነገር የለም። ወልድ የማዕረግ ስም ነውና። የመንፈስ ቅዱስ ስም የሚባል ነገር የለም። ይህ ስሙ ሳይሆን ማንነቱ ነው።

አንድ ቀን ጠዋት በአገልጋዮች ቁርስ ሰዓት ላይ ይህን ጉዳይ እየተናገርኩ ነበር። አንዲት ሴት—ከሥርዓት ውጪ በሆነ መንገድ፣ በእንደዚህ አይነት መልኩ የሚረብሽ ማንኛዉም ሰዉ—"ለአንድ ደቂቃ ብቻ ቆየኝ! ይቅርታ፣ መንፈስ ቅዱስ ስም ነው" አለች።

እኔም፣ "ያ ማንነቱ ነው። ለምሳሌ፣ እኔ ሰው ነኝ። ስሜ ግን ሰው አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም። ማንነት ነው። በርግጥ ማንነትን ይገልጣል። ስም ግን አይደለም።

እንግዲህ አሁን፣ "በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" ካለ እናም አብ፣ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ስም ካልሆነ፣ ታዲያ ስሙ ማን ነው? ስሙን ማግኘት እንፈልጋለን።

69 አሁን ለትንሽ ጊዜ ከታገሳችሁ እና ትኩረት ካደረጋችሁ ሁሉንም እዚህ አንድ ቦታ ላይ ልናገኘው እንችላለን። ለማለት የፈለኩት፣ አሁን...ትንሽ ጊዜ ቆጥቡ። አሁን ማቴዎስ 28፡19ን አስተውሉ። እኔ አሁን ምንም አልልም፣ አንዳንዶቻችሁ እህቶች ወይም ወንድሞች ነገሩን አግኝታችሁታል። አንድ የሆነ ቀን አንድ መጽሐፍ አንስታችሁ ዉስጡን ሳትገልጡ ጀርባውን ተመልክታችሁ "ዮሐንስ እና ማርያም በደስታ ኖረዋል" ብላችሁ ተናግራችሁ ይሆናል። ደህና እንግዲህ፣ ዮሐንስ እና ማርያም ማን ናቸው? ነገሩ ምንድነው...? በደስታ ለዘላለም የኖሩት ዮሐንስ እና ማርያም እነማን ናቸው? ዮሐንስ እና ማርያም ማን እንደሆኑ የምታውቁበት አንድ መንገድ ብቻ ነው። ነገሩ እንቆቅልሽ ከሆነባችሁ፣ ተመልሳችሁ መጽሐፉን አንብቡ። ትክክል ነው? ወደ መጀመርያው ተመለሱ እና አንብቡት። ዮሐንስና ማርያም ማን እንደሆኑ መጽሐፉ ይነግራችኋል።

70 ኢየሱስ ከተናገረ...የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸዉ ደቀመዛሙርት አድርጓቸዉ" ካለ እናም አብ፣ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ስም ካልሆነ እና እንግዲያውስ ነገሩ እንቆቅልሽ ከሆነ፣ ወደ መጽሐፉ መጀመርያ ብንመለስ ይሻለናል።

አሁን ወደ ማቴዎስ ወንጌል የመጀመሪያ ምዕራፍ ተመልሰን ከዚያ እንጀምራለን። እስከ አሥራ ስምንተኛው ቁጥር ጥቅስ ድረስ የዘር ሐረጉን ይሰጣል። አሁን ተመልከቱ፣ አሁን ለአንድ ደቂቃ ብቻ ተመልከቱ። ይህ በቀኝ በኩል ያለዉ አባት ነው፣ ይህ በመካከል ያለዉ ልጅ ነው፣ ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው። እንግዲህ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው። ያ ትክክል ነው? እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው። ሁላችንም ይሄንን እናምናለን? በጣም ጥሩ። እንግዲህ ማቴዎስ 1፡18 እንዲህ ይላል።

እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ ትዉልድ መጽሐፍ ይህ ነዉ:- እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ልጅ ጸንሳ ተገኘች። [እግዚአብሔር አባቱ እንደሆነ አስብ ነበር!] [ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ።]

እጮኛዋ ዮሴፍ ጻድቅ ሆኖ ሳለ፣... ለሕዝብ የመጥፎ ምሳሌ እንዳትሆን ስለወደደ፣ በድብቅ ሊተዋት አሰበ።...

ይህንም ሲያስብ፥ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለው:— የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ የፀነሰችዉ ከመንፈስ ቅዱስ ነዉና ሚስትህን ማርያምን ወደ አንተ ለመውሰድ አትፍራ።

እግዚአብሔር አባቱ ይመስለኝ ነበር። አሁን ወንድሞች ሆይ ኢየሱስ ሁለት አባቶች አሉት? ሊኖሩት አይችልም። ካለዉ ግን ዲቃላ ነዉ ማለት ነዉ። እናም ሀይማኖታችን ምን አይነት ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር አብ እና መንፈስ ቅዱስ አንድ አይነት ራሱን የቻለ መንፈስ መሆኑን አምነህ መቀበል አለብህ። በርግጠኛነት ነው። እርግጥ ነው፣ ያው ራሱ መንፈስ ነው። ይህንን በቀጣይ እናያለን።

ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ እርሱ የራሱን ሕዝብ ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትይዋለሽ።

... ይህ ሁሉ የሆነው በነቢዩ በጌታ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው።

... ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።

ያ ትክክል ነው? እንግዲህ የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ስም ማን ይባላል? በጣም ጥሩ።

71 ለዚህም ነው ጴጥሮስ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያጠምቅ የነበረው።

ነገር ግን እናንተ በሳሮን ጽጌረዳ፣ በሸለቆው ሊሊ ወይም በማለዳ ኮከብ ስም ብትጠመቁ ግድ የለኝም። ይሄም ማዕረግ ነዉ። ልብህ ለእግዚአብሔር የቀና ከሆነ እርሱ ልብህን ያውቃል።

አሁን ግን ... አሁን ያንን ገለጽኩ።

“አሁን” አልኩኝ “አሁን...” ወንድም ስኪዝም፣ “አሁን...!” አለ። እርግጥ ነው። ያ ግን ወንነስን (አንድነትን) ይመስላል፣ እናም እርሱ ለዛ ልቡ የቀና ነዉ። “አሁን፣” አልኳችሁ፣ “አሁን እዚህ፣ አሁን ለእናንተ አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ” ተመልከቱ። እኔም፣ “አሁን፣ እነዚህ... ሁለቱም ሰዎች አንድ አይነት ነገር እንደተናገሩ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ። አሁን ማቴዎስ 'በአብ ስም' አለ። ይሄ ትክክል ነው? በጣም ጥሩ። ጴጥሮስ ደግሞ 'በጌታ ስም' አለ። ማቴዎስ 28:19፣ 'በስመ አብ' አለ። እናም ሐዋርያት 2፡38 'በጌታ ስም' ይላል።”

72 “ዳዊት፡-'ጌታ ጌታዬን አለው።' እርሱ ማን ነበር? አብ እና ጌታ አንድ ናቸው። ዳዊት፡- ጌታ ጌታዬን፡— በቀኜ ተቀመጥ አለው። ተመልከቱ። በአብ ስም - በጌታ ስም።. ማቴዎስም 'በወልድ ስም' አለ ጴጥሮስም 'በኢየሱስ ስም' አለ። ልጁ ማነው? ኢየሱስ። ማቴዎስ 'በመንፈስ ቅዱስ ስም' አለ። ጴጥሮስ 'በክርስቶስ ስም [ሎጎስ]' አለ። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ። ለምን፣ በተቻለ መጠን ፍጹም ነው፣ ተመልከቱ ።”

73 ወንድም ስኪዝም እንዲህ አለኝ....ወንድም ስኪዝም የዋንነስ (ኢየሱስ ብቻ) ግሩፕ ወንድም ነዉ፣ “ወንድም ብራንሃም፣ ይህ ልክ ነው፣ ግን በቃ ይሄ ነው” አለኝ።

“ታዲያስ ይህ ነው” አልኩት። ልክ ነው፣ ተመልከቱ። እኔም “ታዲያ ያ ይህ ከሆነ ያ ደግሞ ይህ ነዉ። ታድያ ስለምንድን ነው የምትጨቃጨቁት? አሁን፣ ”ወንድሞችን ልምከርህ... ከእንግዲህ ሰው ካጠመቅኩ፣ ይሄው በዚህ መንገድ ነው...“ አልኩት።

“አሁን ዶ/ር ኔስ እዚህ አለ...” አልኩ። አንድ ሰው ከጥቂት ጊዜ በፊት፣ እናንተ ወንድሞች፣ ዶ/ር ኔስን እንደምታውቁት ተናግሯል። ደህና፣ እዚህ እላለሁ፣ ወንድም ሂክስ፣ እዚህ እሱ... የዶክትሬት ዲግሪ ያለህ ይመስለኛል። ትክክል ነው? በጣም ጥሩ።“

አሁን፣“ አልኩት፣ ”ዶ/ር ኔስ፣ እዚህ ተቀምጠው ከሆነ.... አሁን፣“ አልኩት፣ ”ከፈለግኩ... አሁን፣ አንድን ሰው ለማጥመቅ ወደ ውሃው ስወስድ፣ አውቄዋለሁ። ልክ እሱ እንዳደረገው ሁሉ“ ”ይህ በስሙ የተጠራባቸው የማዕረግ ስሞች ነበሩ፣ እና...“ አልኩት፣ ”አሁን የጉባኤ እግዚአብሔር ወንድሞች ማዕረጎችን እየተጠቀሙ ነው፣ የዋንነስ ወይም የኢየሱስ ብቻ ወንድሞች ደግሞ ስም እየተጠቀሙ ነው። አሁን፣ “አሁን፣ ሁለቱም ስህተት መሆኑን ላረጋግጥላችሁ ነው፣ እኔ ደግሞ ትክክል መሆኔን!” አልኩት። (እንዴት መሆን እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ። በዚህ መንገድ ጭንቀት ውስጥ ያላችሁ ወንዶች፣ እነሱን ለማዝናናት ትንሽ ጊዜ ትንሽ ቀልድ ነገር ሊኖራችሁ ይገባል፣ ታውቃላችሁ።) እናም “አሁን፣ ሁለቱም ስህተት መሆናቸዉን እና እኔ ደግሞ ትክክል መሆኔን ላረጋግጥላችሁ ነው!”

74 “አሁን፣ ወንድም ኔስን ላከብረው ብፈልግስ? እላለሁ... ወይም ወንድም ሂክስን። 'ሂክስ!' እለዋለሁ። አሁን ይሄ ጥሩ ነዉ? አይደለም፣ 'ዶክተር! ሄይ ዶክ! ብልስ?' ይሄ አክብሮት የጎደለው ይመስላል፣ አይደለም እንዴ? ደህና፣” እንግዲህ፣ “እናንተ ጉባዔ እግዚአብሔር የምታደርጉት እንደዛ ነው፣ ተመልከቱ። እናንተ የጉባኤ እግዚአብሔር ወንድሞች 'በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም' ስትሉ፣ 'በክቡር ዶክተር ስም' እያላችሁ ነዉ።” እንዳልኩት፡- “እናንተ የዋንነስ ወይም 'ኢየሱስ' ብቻ ወንድሞች፣ ስታጠምቁ፣ 'ኢየሱስ ትላላችሁ!'።”.... 'ኢየሱስ ብቻ' የሚለውን አይጠቀሙም፣ ኢየሱስ የሚለዉን ስም ይጠቀማሉ። ብዙ ኢየሱሶች አሉ። ትክክለኛዉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በኢየሱስ ስም የሚያጠምቁ ብዙዎች አሉ። በእርግጠኝነት ይሄን አልደግፍም። አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የለም። ዋናውን ማወቅ አለባችሁ፣ “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ” መሆን አለመሆኑን አጣሩ። በእርግጠኝነት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ብዙ እየሱሶች አሉ። በእርግጠኝነት ክርስቶስ የተቀባዉ ነው።

75 “አሁን፣ ለወንድም ኔስ ተመሳሳይ ነገር ብናገረዉ፣.... 'እንዴት ነህ፣ ኔስ!' ብለዉ ይሻል ይሆን?” እንዳልኩት “እናንተ ዋንነሶች የምትሉት እንደዚህ ነው። ለዚያ የተማረ እና ዶክትሬት ዲግሪ ያገኘውን ሰው በዚህ መልኩ ያለ አክብሮት መጥራት መናቅ አይሆንም? ለዚያ ማዕረግ አጥብቆ አጥንቶ ከሆነ ያንን ማዕረግ ሊሰጠው ይገባል።

እናም እንደገና፣ “እንዴት ነህ፣ ዶክ!” ብለዉ ልክ አይመጣም፣ “አንድ ሚኒስትር ሌላውን ሚኒስትር ሲያነጋግር ሚኒስትር አይለዉም። ራሱም ሚኒስትር ነዉ፣ ሌሎችም ሚኒስትሮች አሉ።” ስለዚህም በትክክል ለመጥራት ማዕረጉ እና ሙሉ ስሙ መጠቀስ ይኖርበታል።

እኔ ግን “አንድን ሰው ወደ ውሃ ስወስድ ወደዚያ ሄጄ እጠይቀዋለሁ.... አወራዋለሁ፣ ስሙን ፣ማን እንደሆነ እና እምነቱን ጠይቀዋለሁ። ከዚያም ጸልያለሁ፣ 'አሁን አባት ሆይ፣ ወደ ዓለም ሁሉ ሄደን አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ አደራ እንደ ሰጠኸን [እናንተ ወንድሞች ይህን ዋና ሃሳብ ታውቃላችሁ]፣ አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።' ብለህ ባዘዝከን መሰረት እንግዲያዉስ፣ 'እምነትህን በመናዘዝህ፣ ኃጢያትህን በመናዘዝህ እና በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለህ እምነት፣ የተወደድክ ወንድሜ ሆይ፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠምቅሃለሁ' ብዬ አጠምቀዋለሁ። እኔ የማጠምቅበት መንገድ ይሄ ነው። ሁሉንም የማዕረግ ስሞቹን— አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ፣ እናም ኢየሱስ እንዲህ ያለበትን ምክንያት አውቃለሁ....

76 አሁን ተመልከቱ፣ ይሄ የማይሆን ከሆነ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እርስ በእርስ ሊጋጩ ይችላሉ። ተቃርኖ ይኖራል፣ እናም ምን ልታደርጉ ነው...? ይህ የቡድሃ እምነት ተከታይ ወንድም ብድግ ብሎ “ይሄኛዉስ?” ቢል ምን ታደርጋላችሁ? አንድ ህንዳዊ ወንድም ሞሪስ ሪድሄድን “ስለ ማርቆስ 16ስ?” ብሎ በጥያቄ ሲያፋጥጠዉ ጥያቄዉን ከዚህ በላይ በተነጋገርነዉ መሰረት መልኩ በአግባቡ መልሶ ዓሣዉን ማጥመድ ነበረበት።

በባዶ እሳ ለማጥመድ መመኮር የለባችሁም። ያ የእግዚአብሔር ቃል ነው! ከእርሱ ጋር ጊዜ ዉሰዱ። ጸልዩ። መገለጡን አግኙ። ሁሉም እርስ በእርሱ አይጋጭም። ይናበባል። አያችሁ። ሁለቱም የሚናገሩት አንድ ነው። ተመሳሳይ ነገር ነዉ።

77 ወጥ የሆኑ ማዕረጎች ብቻ አይደሉም...፣ “አሁን፣ ለይቼ አውቀዋለሁ። እርሱ አብ እንጂ ሌላ አምላክ አልነበረም። እርሱ ወልድ እንጂ ሌላ አምላክ አልነበረም። ያው ራሱ አምላክ። ሶስት ቢሮዎች ናቸው። እግዚአብሔር በአብነት (ዘመን- የአብነት ዘመን ብላችሁ መጥራት ከፈለጋችሁ)፣ ልጅነት፣ እናም አሁን በእኛ ውስጥ ያለው ራሱ አምላክ ነው። 'ከእናንተ ጋር እሆናለሁ (እኔ የሚለዉ የግል ተውላጠ ስም ነዉ)። ከእናንተ ጋር እሆናለሁ።' ስለዚህ አያችሁ፣ ሦስት የአገልግሎት ቢሮዎች እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም። እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ቀጥሎ በነበረዉ ጊዜ ደቀ

መዛሙርቱ በፍጹም ካልተጠቀሙበት፥... እነርሱን አልቃወምም። ትክክል ናቸዉ። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ አንድ ሰው ወደዚህ ወጥቶ በሳሮን ጽጌረዳ፣ በሸለቆው አበባ እና በማለዳ ኮከብ ስም ቢጠመቅ እና ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኙ እንደሆነ ቢያምን፣ "እግዚአብሔር ይባርክህ። ወንድም። ና፣ እንሂድ።" እለዋለሁ። ያ ትክክል ነዉ። ምክንያቱም ልብህ ትክክል ካልሆነ በምንም መልኩ ትክክል አይደለህምና። በትክክል ልክ ነዉ። ልብህ ትክክል መሆን አለበት።

78 እናም "አሁን ተመልከቱ። ወንድም ኔስን ሰላም ለማለት እየሄድኩ ከሆነ፣ 'ሬቨረንድ ዶክተር ኔስ' እላለሁ። በትክክል መባል ያለበት እንደዚህ ነው። አገልጋይ ነው። እንደ አገልጋይነቱ ሊከበር ይገባል። ብዙ ጥናት አጥንቷል፣ እያጠና ነዉ። የዶክትሬት ዲግሪ አለዉ፣ እናም ዶክተር መባል አለበት። ያ ማዕረጉ ነው፣ አያችሁ። ስሙ ግን ኔስ ነው። እናም አሁን፣ 'እንዴት ነህ፣ ኔስ! እንዴት ነህ፣ ዶክ!' ማለት የለብኝም። ይሄ ትክክል አይሆንም። ነገር ግን 'ሬቨረንድ ዶክተር ኔስ' እላለሁ። አያችሁ፣ እኔ የምጠራው እንደዚህ ነው፣ አያችሁ። ማን እንደ ሆነ እዩ፡ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ - ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ።" አልኩኝ።

እናም "በእናንተ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ሰዉ አጥምቄ ቢሆን ኖሮ፣ የማጠምቀው በዚህ መንገድ ነው" አልኳቸዉ። እንደገናም፣ "ወንድም ኔስ፣ ወንድም እስኪዝምን ትቀበለዋለህ?" አልኩት።

እርሱም፡- "በእርግጥ አዎን። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቋል።" አለኝ። "ወንድም ስኪዝም፣ ወንድም ኔስን ትቀበለዋለህ?" አልኩት። እርሱም፡- "በእርግጥ አዎን። በኢየሱስ ስም ተጠምቋል። አለኝ።

እኔም "እናስ ታዲያ ወንድሞች ሆይ፣ ችግራችሁ ምንድነዉ! ለምን ታዲያ ይሄንን ተቀብላችሁ በእነዚህ ምስኪን የሰው ልጆች መካከል የቆሙ የልዩነት ግንቦችን አታፈርሱም....ዋንነሶች ከጉባዔ እግዚአብሔር ጋር በሕብረት ማምለክ የእዉነት ይፈልጋሉ፣...ጉባኤ እግዚአብሔርም ከዋንነሶች ጋር ማምለክ ይፈልጋሉ። ወንድሞች መሆን ያለባቸዉ በዚህ መልኩ ነዉ። ሰይጣን ግን ይዋጋቸዋል..." አልኩኝ።

79 አሁን፣ ወንድሞቼ፣ ምን ለማለት እንደፈለግኩ አይታችኋል? ወደዚያ አንድ ነገር እየመራኋችሁ ነው - ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ! ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አካል አንድነት። አላማዬም ያ ነው። አሁን፣ "አንተን ምለዉ፣ በኢየሱስ ስም አልተጠመቅክም፤ ገሃነም ትገባለህ!" በፍፁም አልልም። አሁን ያ ከንቱ ነው። በሌላ ቀን የሆነውን እነግራችኋለሁ። ከመሰናበቴ በፊት ወደ ቴክሳስ ወርድ ብዬ ነበር፣ በዚህ ያሉ ወንድሞች ምስክሮች ናቸው። ሰባ ሁለት የዋንነስ አብያተ ክርስቲያናት ስብሰባዬን ስፖንሰር አድርገዋል። እናም በዚያ ምሽት ከጉባዔ እግዚአብሔር የመጣዉን ወንድም ፔቲን መድረክ ጋበዝኩት። ነገሩ እዉነት ነው። ዉድ ወንድም ነዉ። የምታውቁት ካላችሁ ወንድም ፔቲ ከቢሞንት ቴክሳስ የመጣ ወንድም ነዉ። እስካሁን ካገኘኋቸው ምርጥ ሰዎች መካከል አንዱ ነው። ሚስቱ የተለወጠች ካቶሊክ ነች፣ እውነተኛ ቅድስት ሴት ነች። እርሱም እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ነው። የጉባዔ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አባል ከሆነዉ ከሮይ ዊድ የተሻለ ጥሩ ሰው ካለ ንገሩኝ! እንደዚህ አይነት ሰዎች ካሉ ስማቸዉን ጥቀሱ። እዚህ ተመልከቱ፣ በዚህ አከባቢ የማውቃቸው እነዚህ ወንድሞች፡ ወንድም... እዚህ ከፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን፣ እና ከጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፣ እና ... ከእነዚህ የሚበለጡ ምርጥ ሰዎች እነማን ናቸዉ? ከጃክ ሙር የተሻለ ምርጥ ሰው ካለ ንገሩኝ? ያንን ንገረኝ። እነሱ የሚጠሩት እሱ ነው የነሱ ናቸው.... አክራሪ አይደለም። በሁለቱም በኩል አክራሪ ታገኛላችሁ። ህዝቡም የሚያተኩረዉ አክራሪ ላይ ነው። ሰይጣንም የሚያተኩረዉ እዚያ ላይ ነው። ሁሉም ግን የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ሰጥቷቸዋል።

የእግዚአብሔር ጸጋ ባይረዳን ኖሮ ሁላችንም በራሳችን ጉዳይ መከራ በጠፋን ነበር። ይህ በትክክል ልክ ነው። የእግዚአብሄር ፀጋ ግን እርስ በእርስ አያይዞናል። "ልባችንን በክርስቲያናዊ ፍቅር ያስተሳሰረ ማሰሪያ የተባረከ ይሁን" ብለን መዘመራችን ምንም አያስደንቅም። እኛ የምንፈልገው ይሄንን ነው።

80 እናም ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? የቤተ ክርስቲያኑ ዋና አስተዳዳሪ ጠራኝ። እርሱም "ትናንት ማታ ያደረግከውን ታውቃለህ?" አለኝ። (በዚያ ሁለተኛዩ ምሽት ነበር)

"ምንድነው?" አልኩት። "አስደናቂ ስብሰባ ነበረን" አልኩት።

"ወደ መድረክ የጋበዝከዉ ሰዉ ሃጢያተኛ ነዉ" አለኝ።

እኔም "አላወኩትም፣ ማን ነበር?" አልኩት።

"ያ ሚስተር ፔቲ" አለ።

"ኦ! ኃጢአተኛ? ለምን? የጉባዔ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ ወንድም ነዉ።" አልኩት። እርሱም፣ "አዎ፣ ነገር ግን በትክክል ስላልተጠመቀ አሁንም ኃጢአተኛ ነው" አለኝ።

እኔም፣ "ወንድሜ፣ ለምን እንደሆነ ጸልየህ ንገረኝ? እርሱ እኮ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል" አልኩት።

እርሱም፣ "ወንድም ብራንሃም፣ ጴጥሮስ ምን አለ? 'ንስሃ ግቡ እና ለሃጢያታችሁ ስርየት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣' ስለዚህ በኢየሱስ ስም እስካልተጠመክ ድረስ ሃጢያትህ ሊሰረይ አይችልም" አለኝ።

"ወንድሜ፣ ያ ፎርሙላ ነው?" አልኩት።

እርሱም "ቀመሩ ይህ ነው" አለኝ። እኔም እንዲህ አልኩት፣ "እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ በሐዋርያት ስራ 10:49 በሰራዉ ስራ የገዛ ራሱን አሰራር አይቃረንም 'ጴጥሮስም ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ።' ከዚያ በፊት በፍፁም አልተጠመቁም ነበር። እንግዲህ እግዚአብሔር ላልተለወጡ ሰዎች እንኳ መንፈስ ቅዱስን ሰጠ።" እኔም፣ "በአለም ላይ አሁን የቆምከው የት ነው?" አልኩት።

81 እርሱም፣ "ምን እንደምናደርግ ታውቃለህ?" አለኝ። "ትንሽዬ ቀለበት እየፈጠርን ነዉ፣ እናም ከሰርክላችን እናወጣችኋለን" አለኝ። እኔ ደግሞ "እኔ ደግሞ ሌላ ሰርክል እሰራለሁ፣ እናም ወደ ሰርክሉ እንደገና በድጋሜ ስብሃለሁ።" አልኩት።

ቀጥዬም "እኔን ከሰርክል ልታወጣኝ አትችልም፣ ምክንያቱም ስለምወድህ። ማድረግ አትችልም። የሚወዱኝ እና በእኔ የሚያምኑ ወንድሞችህ

በጣም ብዙ ናቸው። በምንም መንገድ ወደ እኔ መምጣታቸዉን አያቆሙም። እነርሱ ወደ እኔ ይመጣሉ፣ እኔንም ከእነርሱ መለየት አትችልም። አንተ ብታስወጣኝ እኔ መልሼ ወደ ዉስጥ ስብሃለሁ።" አልኩት። መልሼም፣ "አንተ አንድ ክብ ሰርክል ብትሰራ፣ እግዚአብሔር፣ በጸጋው፣ ሌላ ሰርክል እንድሰራ እና አንተን እንደገና እንድስብህ ያደርገኛል" አልኩት። ይሄ ትክክል ነው። እንደገና ወደ ትክክለኛዉ ቦታ ስባቸዋለሁ።

82 ወንድሜ ሆይ፣ በክርስቶስ ስም፣ ይህን እንድል ፍቀድልኝ (ገባኝ.... እዚህ ጊዜ እንደያዝኩ ይገባኛል። ንግግራችንን ለማቆም ጊዜው ነው፣ ይመስለኛል፣ ግን ይህን ልበል፣ ተመልከት።) ለዚያም ሰዉ እንዲህ አልኩት "ቅዱሳት መጻሕፍትን እስከሰበካችሁ እና ፍቅርም እስካላችሁ ድረስ፣ ይሄንን እስካመናችሁ እና እስከሰበካችሁ ድረስ አብሬአችሁ ሄዳለሁ። ነገር ግን ያልተጻፈ የምትሰብኩከሆነ እና በኢየሱስ ስም ሳይሆን—ኢየሱስ ብቻ — የምትሉ ከሆነ አብሬአችሁ አልሄድም። ከቡርነቶ፣ እንቢ። ምክንያቱም ከብዙ ኢየሱስ ጋር ስለምተዋወቅ። በአፍሪካ እና በተለያዩ ቦታዎች ኢየሱስ የሚባሉ ሰዎችን አውቃለሁ። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚል ቃል የምትጠቀም ከሆነ በዚህ አብሬህ ሄዳለሁ። ምንም አይደለም። ከጎንህ ቆማለሁ። ለመረዳት 'አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ'ን ማስቀደም ያለብህ ይመስለኛል።" "እንዲህ ማድረግ ያለብህ ይመስለኛል" አልኩት።

እርሱ ግን "አይ፣ አይሆንም፣ አይደለም፣ ያ ወደ ሥላሴ ይመልሰናል" አለ።

እኔም፡- "ሥላሴ አይደለም፣ ሶስት አማልክት አይደለም። በሦስት የአገልግሎት ቢሮዎች የተገለጠ አንድ አምላክ ነው! ሥላሴ አይደለም። ሶስት አማልክት የለንም። በእርግጠኝነት የሉም። እንደዚህ ያለ ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አላስተማረም። አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ። "እስራኤል ሆይ፣ ስማ፣ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ"—አንድ አምላክ። የመጀመርያው ትእዛዝ፡- "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በርግጠኛነት አንድ አምላክ ነው እንጂ ሦስት አይደለም። ይህ የካቶሊክ ቅጂ ነው፣ ከካቶሊክ ወደ ሉተራን፣ እያለ ወደ ታች ወዘተ፣ እናም በአጠቃላይ በዚህ ዘመን ሰዎች መካከል ሦስት አማልክት እንዳሉን ይታመናል።

83 እንግዲህ መቼም የማትገኝበት ይሄ ነው... ይህ ወንጌል ወደ አይሁዶች በፍፁም አይሄድም (በሌላኛው ቀን ጠዋት በዚያ ለነበረ አንድ አይሁዳዊ ሚስዮናዊ ትንቢት እንደተናገርኩት)። የሥላሴን አምላክ ወደ አይሁዳዊ በፍጹም አትወስድም። በፍፁም እንደዛ አታደርግም። እርሱ ያልሆነውን...ከዚያ የተሻለ ግንዛቤ አለዉ። ተመልከቱ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ያውቃል። ለአንድ አይሁዳዊ የሥላሴ አምላክ ሆኖ በፍፁም አያዉቅም። ያው ራሱ የጥንቱ ይሖዋ መሆኑን ብታሳውቀው፣ አሁኑኑ ይቀበላል። በእርግጠኝነት! እዉነቱ ያ ነው፣ ተመልከቱ።

እናም ይህን ሁሉ አምናለሁ፣ ዮሴፍ እንደተናገረዉ፣ "ወንድሞች ሆይ፣ በራሳችሁ አትቆጡ፣ እግዚአብሔር ይህን አድርጓልና።" አያችሁ... ነገሩ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እንዲቆይ ነው። ያ ብቻ ነው፣ ምክንያቱም የእኛ የአህዛብ ዘመን ሊጠናቀቅ ነው። አሁን ያን በሙሉ ልቤ አምናለሁ።

84 ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፣ አያችሁ፣ ወደ አንድ የሆነ ቦታ ለመድረስ ነገር እየሞከርኩ ነው። ያም ይህ የሰዎች ስብሰብ፣ የወንዶች፣ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያለው....የኤሚ ማክፐርሰን ቡድን—እርሷ ምን አደረገች? እርሷ መጀመሪያ ዋንነስ ነበረች ፣ አምናለሁ ፣ ከዚያ ወጥታ ጉባኤ እግዚአብሔር ሆነች፣ ከዚያም ወጥታ ብዙም ሳይቆይ እዚህ ራሷን በሌላ መልኩ አደራጀች ፣ ትንሽ ቡድን ዉስጥ ገባች።

እኔ በአ. ኤል. ጃገርስ ስብሰባ ላይ ተቀምጬ ነበር። አሁን ሁላችንም አ ኤል ጃገርስን እናዉቀዋለን። አባቱ የጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን አጠቃላይ ምክር ቤት ምስረታን ድጋፍ አድርጓል። አሁን አ. ኤል. ታላቅ ሰው ነው። ታላቅ ሰባኪ ነው። ብዙም ሳይቆይ በቅርቡ ነገርኩት፣ "ወንድም ጃገርስ፣ ልክ እንዳንተ መስበክ ብችል፣ የፈውስ አገልግሎት እንኳ አይኖረኝም ነበር።" አልኩት። ነገር ግን ያን ሁሉ ደም እና ወይን እና ሌሎች ነገሮችን ያገኘው መጀመሪያ እዚያ ሲጀምር ነው።

85 (ወንድሞቼ ሆይ፣ በዚያ ላይ ስሜቶቻችሁን እየጎዳሁ ከሆነ ይቅርታ አድርጉኝ )።

ምንም አይደለም። እግዚአብሔር ደም እንዲመጣ፣ ወይን እንዲመጣ ወይም ዘይት እንዲመጣ ሊያደርግ ይችላል - የፈለገውን - ነገር ግን ያ ኃጢአትን አያስተሰርይም! በፍፁም ከቡርነቶ። በፍፁም ከቡርነቶ። በእርግጥ አይሆንም! "የእግዚአብሔር ቤዛ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ኃጢአት እስከማትሰራ ድረስ እስክትድን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ኃይሉን አያጣም!"

"ወንድም ጃገርስ..." አልኩት... ደወልኩለት (ከክርስቲያን ነጋዴዎች ጋር ነበርኩ) እናም "ወንድም አ.ኤል..." አልኩት።

እርሱም፣ "በአለም ውስጥ የት ነው ያለኸዉ?" አለኝ። እኔ እዚያ ትንሽ አሮጌ ርካሽ ሞቴል ውስጥ ነበርኩ፣ እናም እርሱ፣ "ከእዚህ አስወጡኝ ነዉ ምትለኝ?" አለኝ።

እኔም፣ "ይህ የኔ ፍላጎት ነው። ወደ አንተ ስመጣ" "ምን አደረግክ? ስታትለር ሆቴል አስገብተህኛል፣ እና ጥግ ላይ መቆም ነበረብኝ። ጠረጴዛው ላይ አስቀምጠኸኛል፣ እና የትኛውን ቢላዋ መጠቀም ወይም አለመጠቀም እንዳለብኝ አላውቅም ነበር፣ እኔም ኮት ሳለብስ ወደዚያ ወረድኩ፣ ሊያስወጡኝ ፈለጉ።" እናም "ራሴን እንዴት እንደምይዝ አላውቅም" አልኩት።

እርሱም፡- "እነሱ ይህን ለማድረግ በጣም ድሆች ከሆኑ ወደዚያ እወስድሃለሁ።" አለኝ

"በፍፁም ከቡርነቶ" አልኩት። እናም፣ "ማድረግ የምፈልገው ለዚያ የምትከፍል ከሆነ ከአንተ ጋር ስቴክ መያዝ ነው።" አልኩት።

እርሱም "እሺ" አለ።

እናም ከዚያ ወደ አንድ ቦታ ወጣን፣ እናም ተቀመጥን፣ እኔም "ወንድም ጃገርስ፣ በርግጥ ያንተን... አደንቃለሁ" አልኩት። በጣም የምወደው ጓደኛዬ፣ ውድ ወንድሜ ነው። የእርሱን ትንሽ በራሪ ወረቀት ይዤ ነበር፣ ከባህር ማዶ የመጣች ያቺ ደም በእጆቿ እና በነገሮችዋ ላይ ያለባት ሴት ነበረችበት። ስለዚህ እዚህ አገኘሁት። አንድ ጊዜ እንዲከደው ፈልጌ ነበር፣ ከዚያ ግን በወረቀቱ ላይ አገኘሁት፣ ታውቃላችሁ።

86 እኔም፣ "ቀጥታ ወዴት እየሄድክ እንደሆነ አስተዉያለሁ፣ ታላቅ ሪቫይቫል ልታደርግ ነዉ።" አልኩት። በርግጥ ሃሳቡን ለመጀመር ያህል ነዉ እንጂ የቢዝነስ ሰዎች በዚያ እየጠበቁኝ ነበር ....

መንፈስ ቅዱስ ነገሮችን መድረክ ላይ ብቻ የሚገልጥ የሚመስላቸዉ ብዙ ሰዎች ያሉ ይመስላል፣ ወንድሞች ሆይ፣ ከመድረክ ዉጭ በተለያዩ ቦታዎች ምን እየተካሄደ እንዳለ ሊነግረኝ የማይችል ይመስላችኋል? ቃል በቃል ልነግራችሁ እችላለሁ፣ እናም በወንድም ካርልሰን እና በዚህ ሌላኛዉ

ወንድም ልታረጋግጡ ትችላላችሁ፣ ትናንት በስብሰባ ላይ ተቀምጬ ለእነዚህ ወንድሞች ዛሬ ጠዋት ምን እንደሚሆን ነገርኳቸው። ያ ትክክል ነው። በትክክል። ተመልከቱ፣ ምክኒያቱም መንፈስ ቅዱስ ቀሰቀሰኝ እና "በመስኮት አጠገብ ቁም" አለኝ። መስኮቱን ተመለከትኩኝ፣ እናም እርሱ በትክክል ይህንን አሳየኝ። "አሁን ወንድሞቼ..." አልኩኝ። (ወንድም "በትክክል ልክ ነህ") ይላል። ለምንድነው፣ ሊያውቁት ይገባል።

87 ብዙም ሳይቆይ በቅርቡ አንድ ሰው እዚህ ቻታካ (Chautauqua) ተነሳና "ወንድም ብራንሃም ነቢይ ነው" አለ። ነብይ ነኝ አልልም ። እርሱ ግን፣ "ወንድም ብራንሃም በመለየት መንፈስ ውስጥ ሲሆን ነብይ ነው፣ ነገር ግን፣" "አህ፣ ትምህርቱ መርዝ ነው። ተጠንቀቁ።" አለ።

አሰብኩ...የተማረ ሰው እንዲህ ያለ ነገር ይናገራል። ነብይ ማለት ምን ማለት ነው? "የቃሉ መለኮታዊ ተርጓሚ" የጌታ ቃል ወደ ነቢዩ መጣ።

ነገር ግን ያ እዚህም ሆነ እዚያ አልሆነም...አያችሁ። ግን ለማንኛውም ወንድም ጃገርስ..."ስለዚያች ደም በእጇ ስላለዉ ሴት አይቻለሁ።" አልኩት።

"አህ፣" አለ፣ "ወንድም ብራንሃም፣ ያ እስካከዛሬ ካየኸው በጣም አስገራሚ ነው።"

እኔም፣ "ወንድም ጃገርስ፣ እወድሃለሁ። በመጀመሪያ፣ እጄን በእጅህ ዉስጥ እንድታስገባ እፈልጋለሁ። ወንድማማቾች ነን እንበል።"

እርሱም፡- "እርግጥ ነው። ምንድነው ነገሩ?" አለኝ።

እኔም፣ "እኔ ከማውቃቸው ከባድ ሰባኪዎች ዉስጥ አንተ አንዱ ነህ። አንተ ለእግዚአብሔር እንዴት ያለ መሣሪያ ነህ!" አልኩት።

እርሱም፣ "አመሰግናለው ወንድም ብራንሃም። አንተ በእርግጥ ትሑት ነህ።" አለኝ።

እኔም እንዲህ አልኩት፣ "ይህን የምለው ትሁት ለመሆን አይደለም። ይህን የምለው ስለማምን ነው። አንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነህ። ግን፣" አልኩት፣ "ወንድም ጃገርስ፣ ከ...በቀር..... በጣም እየሮጥክ ነው። ለምትናገረው ነገር ምንም ሚዛን የለህም። ..."

88 እናም እናንተ የጉባዔ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እና ሌሎች፣ በእነዚህ የፈውስ አገልግሎቶች ላይ ያለባችሁ ችግር ይሄ ነው። አልወቀሳችሁም። ብዙ የተጠሩ አሉ.... እናም ቶሚ እዚህ ጥሩ ወንድም ነው፣ እናም ምን ያህል ጠንካራ አቋም እንዳለዉ እናውቃለን። ነገር ግን ዛሬ በመለኮታዊ ፈውስ ስም በምድሪቱ ላይ ብዙ ነገር አለ፣ በከተማው ውስጥ ስብሰባን ስፖንሰር ማድረግ ባትፈልግ ምንም አያስደንቅም። መጥተው ህዝቡን አድምተዉ ይሄዳሉ ምን አገኙ? አንተ በራስህ መድረክ ለህዝቡ ከምትሰጠዉ ትንሽ አስበልጠዉ አልሰጡም። ወንድሞቼ፣ ልክ ናችሁ። ልክ ነህ እያልኩህ ነዉ።

ግን የማርቲን ሉተርን ታሪክ እያነበብኩ እንደነበረው ነው። እንዲህ ይላል፣ "ማርቲን ሉተር የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን በመቃወም [ታሪኩን አንብበሃል]፣ ነገር ግን ማርቲን ሉተር የእሱን መነቃቃት ተከትሎ ከነበረው አክራሪነት ሁሉ በላይ ራሱን መያዙ እንቆቅልሽ አልነበረም። በዚያ ሚስጥር ነበረ። ክስተቱ ሲፈጸም ያልተገረዙት ልክ በግብፅ እንደነበረው ይከተላሉ።እናም ሁልጊዜም በምድሩ ላይ ችግር አስከትሏል። እኛ እዚያ ስንወጣ - ቆሬ ያስነሳው እና እግዚአብሔር ያጠፋው እንደነበረ እናውቃለን። ወንድሞቼ ግን አልወቅሳችሁም።

89 ወንድም ጃገርስ እዚያ ተቀምጦ መንፈስ ቅዱስ ያንን እያደረገ እንደሆነ ሊነግረኝ ሞከረ እና እንዲህ አለ... ከዚያ በኋላ በእኔ አገልግሎት ዙርያ እየየፈ እንዳለ ነገረኝ ። እኔም፣ "ወንድም ጃገርስ፣ አሁን፣" አልኩት፣ "እኔ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፣ አንተ ደግሞ የስነ መለኮት ትምህርት ዶክተር ነህ፣ እናም ጠበቃ ለመሆን ተማርክ። አንተ ያደከዉ በንጹሕ፣ ጨዋ በሆነ ቤተክርስቲያን-በጉባዔ እግዚአብሔር ውስጥ ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን እንዲመሰረት አባትህ ድጋፍ አድርጓል። አንተ ደግሞ ወደ ሌላ እየገተተክ ነው፣ ያ የራስከ ጉዳይ ነዉ። ይህን ማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም ሌላ ሰው የራሱ ጉዳይ ነው። እዚያ ምንም አይነት መስመር አላሰምርም፤ ነገር ግን እንዳንተ ያለ የእግዚአብሔር መጠቀሚያ የሆነ ሰዉ - በሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ መመለስ የሚችል ሰዉ- አገልግሎቱን በስሜት ላይ መገንባት የለበትም!"

እኔም፣ "ወንድም ጃገርስ፣ እንደዚህ አይነት አምድ ትገነባለህ፣ ለዛ ደግሞ ምንም ሚዛን ከሌለህ፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይወድቃል። እናም ስለምትናገረው ነገር ሁሉ ቅዱሳት መጻህፍት ሊኖሩህ ይገባል።" አልኩት።

እርሱም፣ " ቅዱሳት መጽሐፍት አሉ" አለ።

"አሳየኝ!" አልኩት።

እርሱም፣ "እሺ፣ ወንድም ብራንሃም፣ መንፈስ ቅዱስ ያንን እያደረገ ነው" አለ።

እኔም፣ "መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ላይ ደም እንዲወጣ አድርጓል የሚለውን መፅሃፍቱን አሳዩኝ፣ እና የመሳሰሉትን። ብቻ አሳየኝ-ዘይት ከዉስጣቸዉ ይፈስሳል። ዘይት ለመለኮታዊ ፈውስ ነው ብለሃል፣ እናም የሴት ደም ለአሕዛብ መዳን ይሆናል ብለሃል።" እኔም "እንዲህ ከሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምን ሆነ?፤ የሚቃወመውም ሁሉ 'ጸረ' ነው። ይቃወማል። "የክርስቶስ ተቃዋሚ ትምህርት ይሆናል" አልኩት።

"አህ፣ ወንድም ብራንሃም፣ አንድ ቀን ትማራለህ" አለው።እንዲህ አልኩት፣ "እንደዚያ እንዳልማር ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን፣ ወንድሜ፣ "እወድሃለሁ፣ አንተ ወንድሜ ነህ" አልኩት። "ወንድም ጃገርስ፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መመለስ ወደማትችለዉ ሁኔታ ዉስጥ ልትወድቅ ነው! ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ተመለስ እና ከወንጌል ጋር ኑር!" እናም "ወንጌልን በስሜቶች ላይ አትገንባዉ" አልኩት። ብያለው...

90 አሁን ነገሩን ተቀብሏል... ወደ ዘላለም ሕይወት እያጠመቀ ነው። ታውቃላችሁ፣ ባጠመቅክ ቁጥር፣ ወደ ወጣት ሴት ወይም ወንድ ትመለሳለህ። አሁን ያ ይሆናል .... በጭራሽ አይሞትም፣ ስለዚህ አሁን በእጁ መጨረሻ ላይ ነው። እና እነርሱ ከሙት ባህር የወጡ የቫይታሚን ክኒኖች... !

አየህ ወንድሜ፣ ግን ያ ራሱ የሆነው እሱ ነው። በእነዛ ትንንሽ ስሜቶች ትጀምራላችሁ፣ እና እናንተ እነዚን አብያተ ክርስቲያናት ያላችሁ ሰዎች፣ እንደዚህ ያለ ነገር ወደ ከተማው እንዲገባ ትፈቅዳላችሁ። ታዉቃለህ፣ ዲያቢሎስ አታላይ ነዉ። እንደዚህ በሚመሳሰሉ ነገሮች ዉስጥ ዘሎ ይገባል። ያባብሰዋል። ሰዎችን ያቆስላል፣ እና በቤተ ክርስቲያን እና ነገሮች ላይ ውዥንብር ይፈጥራል። ግን እንደዚያ አይሆንም።

91 አሁን፣ እዚህ፣ ምንም ያህል ትክክል ብትሆኑ፣ ወንድሞቼ፣ እኛ የምንወድቀው እና የምንሳሳተዉ አንድ ነገር እዚህ አለ። አሁን ይህን ብዬ ጨርሳለሁ። የቱንም ያህል ትክክል ብሆን፣ እና የቱንም ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብሆን፣ እና ስለ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል ባውቅ፣ ለጠቅላላው የሰው ዘር የእግዚአብሔር የፍቅር መንፈስ በልቤ ውስጥ ከሌለኝ ሲመጀመር ከመሰረቱ ተሳስቻለሁ።

አሁን፣ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ላይ፣ “ምንም እንኳን እዉቀት ቢኖረኝ፣[አያችሁ] የእግዚአብሔርን ምሥጢር ሁሉ ባውቅ፣ ፍቅር ወይም በጎነት ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገርም [ከእግዚአብሔር ጋር የሚናገሩት ሁልጊዜም ሊተረጎም የሚችል ነዉ]። በሰዎችና በመላእክት ልሳኖች [እዉነተኛ ልሳኖች] ብናገር በጎነት [ፍቅር] ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። ስለዚህ፣ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ሁሉ አውቄ ገልጬ ሁሉንም በአንድ ላይ እንዲገጣጠም ባደርግ፣ ፍቅርም ከሌለኝ ምን ጥሩ ነገር ያደርጋል? እና እኔ ....

92 ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- “...እርስ በእርስ ብትዋደዱ እናንተ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ ያውቃሉ...” ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ለዋንነስ ቤተ ክርስቲያን ፍቅር ሲኖራቸው፣ ዋንነስ ለጉባኤ እግዚአብሔር ፍቅር ሲኖራቸዉ፤ አላማችን ትክክል ቢሆን ወይም ባይሆን እርስ በርሳችን ፍቅር ካለን ትክክል ነን። የልብ መሻት የተሳሳተ እስከሆነ ድረስ ... አላማው የተሳሳተ ነው፣ ይልቁንም ፣ ሲጀመር ከመሰረቱ ስህተት ነዉ። ትክክል ነዉ እንዴ? በፍጹም አይደለም። እነሆ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይደለሁም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ያንን እናውቃለን።

በልሳኖች በመናገር አምናለሁ። አሁን፣ አንድ ሰው፣ “ወንድም ብራንሃም በመጀመርያዉ ምልክት አያምንም።” አለ። ይሄንን የተሳሳተ ሃሳብ ላርምላችሁ እፈልጋለሁ፣ ተመልከቱ። ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። አንድ ሰው ክርስቶስን ሲቀበል የመንፈስ ቅዱስን ክፋይ ክፍል እንደሚቀበል አምናለሁ ምክንያቱም ኢየሱስ በማቴዎስ ምዕራፍ አሥራ ሁለተኛው ... አምስተኛው ምዕራፍ እና ሃያ አራተኛው ቁጥር ላይ እንዲህ አለ .... አይደለም፣ በቅዱስ ዮሐንስ 5፡24 ላይ እንደሆነ አምናለሁ። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ “ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው [አንድ የዘላለም ሕይወት ፎርም ወይም መልክ ብቻ አለ] ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገር እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።”

93 አሁን ማንም ሰው ራሱን መጥራት እንደማይችል አምናለሁ። እግዚአብሔር ሊጠራው ይገባል። እናም በእውነት እግዚአብሔር ከጠራው .... አሁን፣ ብዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን፣ ወንድሞች፣ እግዚአብሔር እንደጠራቸው አድርገው ያስባሉ፣ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ሕይወታቸውን ታዩታላችሁ ... ታውቃላችሁ። እግዚአብሔር ከጠራችሁ ግን ለምን በዚያ ትሆናላችሁ፣ ለምን በዚያ ትቀመጣላችሁ። እናም አሁን፣ ያ የባፕቲስት ወይም የመጥምቃዉያን ትምህርት አይደለም፣ ያንን ታዉቃላችሁ፣ አያችሁ። እጅ በመጨባበጥ በሚገኝ ዘላለማዊ ደህንነት እና ያንን ሁሉ ነገር አላምንም። በፍፁም በዛ አላምንም። ያንን ማመን ከፈለጉ፣ ደህና፣ ጥሩ ነው። እስከ አሁንም ድረስ ወንድሞቼ ናቸው እላለሁ።

94 ዛሬ ጠዋት፣ አንድ ቁራጭ ኬክ መብላት ብፈልግ- በእርግጥ የእራት ሰዓት እየተቃረበ ነው- እኔ ቼሪ ልበላ እችላለሁ፣ እናንተ ደግሞ ፖም ትበላላችሁ፣ ነገር ግን ሁለታችንም ኬክ እየበላን ነው፣ አያችሁ። ስለዚህ ሁላችንም ኬክ እየበላን እስከሆንን ድረስ ምንም ልዩነት አያመጣም። እንደዚያ ነው የምናምነው።

ዋንነስ መሆን ከፈለጋችሁ ዋንነስ ሁኑ። ጉባኤ እግዚአብሔር መሆን ከፈለጋችሁ ጉባኤ እግዚአብሔር ሁኑ። የፈለጋችሁትን- ለምሳሌ ባብቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን- መሆን ትችላላችሁ። ብቻ እናንተ በውስጡ ክርስቲያን ሁኑ፣ አያችሁ። እናም ለራሳችሁ እዉነተኛዉን መንገድ ፈልጉ፤ ነገር ግን እርስ በርሳችሁ አትከራከሩ፤ ምክንያቱም እነዚህ ትንንሽ ነገሮች ሁሉ ወደ በአንድነት ይመጣሉ። ትክክል ነው። ሁሉም አንድ ሆነዉ በመጨረሻ ወደ አንድ ቦታ ይመጣሉ።

እናም ምንም ብናደርግ፣ ምን ያህል ተአምራት ብንሰራ፣ ምን ያህል ተራሮች ማንቀሳቀስ ብንችል፣ ወይም ምንም ይሁን ምን፣ ወደምናፈቅረዉ ወይም ወደምንወደዉ ወደ አንድ ቦታ መምጣት እስክንችል ድረስ- እምነት አይኖረንም - ግን እርስ በርሳችን እንዋደዳለን። እያንዳንዱን ወንድም ስንወድ...የየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ቢሆንም...እንወደዋለን።... ማስመሰል ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ሃሳብ መሆኑን ስለምናውቅ ጭምር ነዉ...ማድረግ ስላለብን እናደርገዋለን። እርስ በርሳችን እንዋደዳለን። ከዚያም በትዕግሥት እርስ በርሳችን እንታገሳለን።...

በቆላስይስ 3፣9 አካባቢ፣ እዚያ ውስጥ የሆነ ቦታ እንደሆነ አምናለሁ.... ጥቅሱን ተሳስቼ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን “ክርስቲያን ከሆንን በኋላ መቅናት ወይም መመቅኘት አይገባም” ይላል። እርስ በርሳችን ለመከባበር ወይም ክብር ለመሰጣጠት የምንሞክር ከሆነ እምነት ሊኖረን አይችልም። አያችሁ፣ ያንን ማድረግ አንችልም። እምነት ሊኖረን አይችልም። እግዚአብሔርን ማክበር አለብን። እሱን አክብሩት። በወንድሞች ማመን በእርግጠኝነት ፍቅር ነው። አክብሮት እና ክብር ግን ለእግዚአብሔር ነው። ነገር ግን እርስ በርሳችሁ እምነትና በራስ መተማመን ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም አትዋሹ፤ ተመልከቱ። እርስ በርሳችሁ አትዋሹ። ዛሬ ጠዋት እንደምወድህ ከነገርኩህ፣ የእዉነት መሆን አለበት። ካልሆነ ግን ግብዝ ነኝ! በትክክል ያ ነው።

95 አሁን፣ ወንድሞች ሆይ፣ በዚህች ጉዳይ... አሁን፣ ወንድም ቶሚ፣ በዚህ ሁርያ ብዙ እንዳላልኩ አስባለሁ። ወንድም ቶሚ በአንድ ሰከንድ ውስጥ የሚናገረው ይኖረዋል።

እኔ ግን ይህን ልናገር እችላለሁ። ወደ እናንተ መካከል ስመጣ፡ እግዚአብሔር አባታችን ማርያም የምትባል ድንግል ሴትን እንደጸለላት፣ በውስጧም ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደውን የደም ሴል እንደፈጠረ፣ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ራሱን በሥጋ የገለጠበት ድንኳን እንደሆነ እንዲሁም ራሱን በእኛ መካከል እንደተገለጠ አምናለሁ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ አለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር። ያ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሰዉ ምድር ለማምጣት የተፈጠረዉ የደም ሴል በቀራንዮ ለኃጢአታችን ስርየት እንደተቆረጠ እና መንፈስም ከእርሱ እንደወጣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ላይ ተመልሶ እንደመጣ አምናለሁ። ምክንያቱም እኛ በቡድን ሆነን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድንሆን ክርስቶስ፣ መንፈስ ቅዱስ የሆነዉ ክርስቶስ፣ ሎጎስ የሆነዉ ክርስቶስ -አሁን በእኛ ውስጥ ነዉ፣ በጥምቀት የሆነ መንፈስ ቅዱስ፣ እኛን እየሠራ .... ክርስቶስ ራሱን ለየ፣ ለእያንዳንዳችን ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።

96 እናም በቅርቡ .... ፈረስ ጋልብ ነበር። ፈረስ ጋላቢ እንደሆንኩ ታዉቃላችሁ። አባቴ ጋላቢ ነበር፣ ታላቅ ተኳሽም ጭምር። እጋልብ ነበር። በአራፓሆ ሸለቆ ከብቶች እንጠብቅ ነበር። ከአራፓሆ መልከዓ ምድር በላይ ያለውን አስቸጋሪዉን ወንዝ ማለቴ ነው። የሄሬፎርድ ማህበር ያንን ሸለቆ ያለማሉ። በዚያም ሸለቆ ከብት አርቢዎቹ የሚያመርቱት ብዙ ሣር አላቸው። እናም ከብት አርቢዎቹ አንድ ቶን የደረቀ ሳር ሲያመርቱ እዚያ ከእስቴስ ፓርክ በታች ባለው የግጦሽ መስክ ላይ ላም ማርባት ትችላላችሁ። ላም ማርባት ትችላላችሁ። እናም ያ አካባቢ የእኔ ታላቅ አደን ስፍራ ነው፣ በእዚያ ለብዙ ዓመታት አድኛለሁ። በጠመዝማዛዉ መንገድ እሄዳለሁ እናም አንዳንዴ ሲያዳልጠኝ እወድቃለሁ። ደግሞ ተነስቼ ቀጥላለሁ፣ እና እዚያ ጫፍ

ለመድረስ ሽንተረሩን እጋልባለሁ፣ ምክኒያቱም መጋለብ ወዳለሁ።

እናም በዚያ ከፍታ እና ዝቅታ ባለዉ ሸለቆ ዉስጥ ከብቶቻቸውን የማሰማራት መብት ያላቸው ብዙ ከብት አርቢዎች አሉ፣ እናም በፀደይ ወቅት ብዙ ጊዜ ከብቶቻቸዉን ሰብስበው ወደዚያ ላይ እንዲሮጡ ረድቻቸዋለሁ። እናም በየቦታዉ ያሉ የግል ንብረቶች ላይ ወደ ኋላ መመለስ የማይችሉበት ተንሸራታች አጥር አለ ፣ እናም ጠባቂው እዚያ ቆሞ እነዚያን ከብቶች ሲገቡ ይቆጥራቸዋል ፣ በዚያ ብዙ ቀን ተቀምጫለሁ፣ ብዙ ሰዓት። የአቶ ግሪሜ ከብቶች ሲያልፍ እመለከታለሁ - የአልማዝ አሞሌ ነበረው። የእኛ የቱርክ ትራክ ነበር፣ እና እነሱ ከእኛ በታች ትሪፖድ ነበራቸው፣ እና ጄፍሪስ፣ ወዘተ።

ከዚያም ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት... እግሬን የኮርቻው ቀንድ ላይ አድርጌ ቁጭ ብዬ ያንን ጠባቂ እዚያ ቆሞ እነዚያን ከብቶች ሲቆጥር አያለሁ። አንድ ነገር አስተውያለሁ። በእርሱ ላይ ላለው የምርት ስም ብዙ ትኩረት አይሰጥም፣ ግን የእዉነት የሚፈልገው አንድ ነገር ነበር። እርሱም የደም መለያው ነበር። የዳበረ ሄሬፎርድ መሆን አለበት አለበለዚያ ከዚያ አጥር በስተጀርባ መሄድ አይችልም ፣ ግን የምርት ስሙ ብዙ ለውጥ አላመጣም። በፍርድ ቀንም እንደዚሁ ይመስለኛል። እርሱ የእኛን መለያ አይመለከትም፣ የደም መለያውን ግን ይፈልገዋል።

97 ወንድሞቼ ሆይ፣ ስህተቶችን ሰርቻለሁ፣ ብዙ ስህተት የሆኑ ነገሮችን ሰርቻለሁ። እናም በማንኛውም በመጣሁበት መንገድ ...ወይም እኔ የተናገርኩትን ሰምታችሁ ወይም አስተያየት በሰጠሁበት ጉዳይ የተከፋችሁ ወይም ዛሬ ጠዋት መጥፎ ነገርን ከተናገርኩ እንደ ክርስቲያን ወንድም ወይም እህት ይቅርታ ጠይቃለሁ። እንደዛ ማድረግ አልነበረብኝም። ልቤን የገለጥኩላችሁ ነገሩን እንድናዉቀዉ ነዉ።

የሚጠመቅ ሰዉ ካለ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ራሳችሁ አጥምቁ። እኔ...ግን አላደርገውም። ማጥመቅ ካለብኝ ግን የማጠምቀዉ በነገርኳችሁ መንገድ ነዉ። ይሄንን ከእናንተ አንዱ ሊቀበለዉ እና ሊተገብረዉ ይችላል። ስለዚህ እነርሱ— በአብ፣ በወልድ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚያጠምቁትን ሰው ወስዳችሁ፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደገና አጥምቁት። ስለዚህ እኔ የማጠምቅ ከሆነ ...እስካሁን ግን አላደረግሁትም። እኔ የማጠምቀው በራሴ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው፣ እናም በዚያ ያሉ ሰዎች ብቻ ናቸው፣ በቤተክርስቲያኔ ያሉ ሰዎች የሚጠመቁበት መንገድ ይህ ነዉ። ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ካያችሁ፣ ይህ የድሮው የሚስዮናውያን መንፈሳዊ ሥርዓት ነው... የጥንት የሚስዮን ባፕቲስት ሥርዓት። እናም አሁንም ቢሆን መሆን ያለበት ያዉ ነዉ።

98 በመለኮታዊ ፈውስ አምናለሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አምናለሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ በልሳኖች መናገር አምናለሁ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ በሰጠው ስጦታ ሁሉ አምናለሁ። እኔ 100% እቀበላለሁ፣ እፈልጋለሁም፣ ነገር ግን.... ዛሬ በዙሪያችን ባለው እጅግ በጣም ብዙ የዉሸት ፈውስ አላምንም። የለሁበትምም።

እዚህ ላይ አስተያየት መስጠት እፈልጋለሁ። ከተወሰነ ጊዜ በፊት አንድ ወንድም ነበር፣ እናም እንደ እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ የምመለከተው ውድ ወንድሜ ቶሚ ሂክስ አይደለም። በሌላ አገር የሚኖር ሌላ ሰው ነበር። በዚህች አገር ውስጥ እንደምታዉቁት "የእግዚአብሔር ሱፐር-ዱፐር ፈዋሽ; ሱፐር-ዱፐር ፈዋሽ" ነበሩ። እናም ሰውዬው የፈዉስ ፕሮግራም ካደረገ በኋላ... ከሉተራን ቤተ ክርስትያን ደብዳቤ ደረሰኝ። አሁን በዚህ ያለችዉ ፀሀፊዬ ታዉቃለች። ፋይላችን ውስጥ አለ። የሰውየውን ስም አልጠራም፤ ምክንያቱም ክርስቲያናዊ አይደለም። ምንም እንኳን በሰዉየዉ ሃሳብ ባልስማማም ማለት ነዉ። ግን ያ ፍጹም ትክክል ነው። እወደዋለሁ። ወንድሜ ነው።

99 ነገር ግን ልክ የሆነ ዓይነት ስሜት ዉስጥ እንዲገቡ የሚያደርግ፣ ወይም የመገረፍ ስሜት፣ ወይም የሆነ ነገር ወይም ሌላ ነገር የሚፈጠርበት ሁኔታ ይፈጠራል። ያ ደግሞ ጥሩ አይደለም። ወንድም፣ የሰውነት እንቅስቃሴ በጥቂቱ ይጠቅማል። እናም እኚህ የሉተራን አገልጋይ ለዚህ የፈዉስ አገልጋይ መልሰው ደብዳቤ ፃፉ፣ እናም እንዲህ አሉ፡- "እናንተ እዚህ የምትመጡ አሜሪካውያን ወንጌላውያን፣" አሉ "ለሁሉም ሰው ከሚሆን ሱፐር-ዳፐር ፈውሳችሁ ጋር ....." (እናም አሁን፣ ይህ ትንሽ ነገር ይመስለኛል፣ ግን እንደዚያ ማለቴ እንዳልሆነ እግዚአብሔር ያውቃል። "ግን" አለ፣ "ያቺ ትንሽ ሕፃን ዲቦራህ ስታድስኬቭ ስትሞት ... ህፃኗ ስትቀዘቅዝ እና ስትሞት እናትየዋም በዚያ ቀን በካሊፎርኒያ ነበረች። ያቺን ህፃን በወንድም ብራንሃም እቅፍ ውስጥ ሲያስቀምጡ፣ እናም በዚያ ቆሞ ለህፃኗ ሲጸልይ፣ እናም ህፃኗ መጮህ እና መማታት ስጀምር፣ ከዚያም መልሶ ለእናትየዋ ሰጣት።"

100 የሜክሲኮን ጉዳይም ያውቅ ነበር፣ ይህም ....የሙሉ ወንጌል የቢዝነስ ሰዎችን... መግለጫ መሰረት ማድረግ እንችላለን። ከዶክተር የተገለጸ ነገር ሊኖራችሁ ይገባል። ያ ትንሽ የሜክሲኮ ህጻን በዚያ ቀን ጠዋት ዘጠኝ ሰአት ሲሞት እና በምሽቱ አስራ አንድ ሰአት ሲሆን ዶክተሩ መሞቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ጻፈ። ብዙዎቻችሁ የጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ወንድሞች የምታውቁት ወንድም እስፒኖዛ ነዉ ሐኪሙ የፃፈዉን የህፃኑን መሞት የሚገልጸዉን ደብዳቤ የተቀበለዉ።

በሕዝቡ ላይ (በሜክሲኮ ሲቲ 20,000 የሚሆኑ ካቶሊኮች ወደ ክርስቶስ ሲመጡ) ራዕይ አየሁ። እኔም "ይህን ዝም ብለህ አትውሰድ። ያንን ልጅ አላውቀውም። እዚህ አንድ ራእይ አይቻለሁ። እናም ቢሊ ከሠላሳ ወይም አርባ ከሚሆኑ አስተናጋጆች ጋር እየሞከረ ነበር—ትንሿን ሴት ከዚያ ሕፃን ጋር ከጸሎት መስመር ማስወጣት አልቻለም። በእግራቸው እና በሁሉም ነገር መካከል ትሮጥ ነበር።

ስለዚህ በመጨረሻ ጃክ ሙርን ላክሁት። "ሂድ ጸልይለት" አልኩት። እዚህ ወደ ውጭ ተመለከትኩ፣ እና አንድ ትንሽ የሜክሲኮ ሕፃን ፈገግታ አየሁ። እኔም፣ "አንድ ደቂቃ ቆይ። ወደዚህ አምጣው" አልኩት። እናም እጄን በዛ ብርድ ልብስ ላይ ሳደርግ .... ቀኑን ሙሉ ዝናብ ነበር። እነርሱም ከጠዋት ጀምሮ እዚያ ቆመው ነበር፣ እናም በዚያ ሌሊት አስራ አንድ ሰዓት ያህል ነበር። እናም እጆቼን በትንሹ ህጻን ላይ ጫንኩ። መንፈራገጥ እና መጮህ ጀመረ። እነርሱም መጮህ ጀመሩ።

101 ከዚያም፣ ሕፃኑን አውርደው የዶክተሩን መግለጫ አገኙ። እናም ወደ ሐኪሙ ሄደው እንዲህ አለ፡- "ሕፃኑ በሳንባ ምች በሽታ ምክኒያት መሞቱን ያረጋገጥኩት ዛሬ ጠዋት ዘጠኝ ሰዓት ላይ ነው።" እናም ስለዚህ እነዚያ ነገሮች እውነት ናቸው። የሃኪም መግለጫዎች ናቸው። ታማኝ መሆን አለበት። ስለማንኛውም ነገር ሁል ጊዜ ሐቀኛ እና እውነተኛ መሆን አለብን። ምንም አትጨምሩበት... ምን እንደሆነ ብቻ ይሁን። እግዚአብሔር በምንም ነገር ላይ የማንንም እርዳታ አይፈልግም፣ አያችሁ። እርሱ አምላክ ነው።

102 እናም እንዲህ አለ... "አሁን ግን ይህች እናት አሜሪካ የሚገኘውን ወንድም ብራንሃምን ደውላ በስልክ 'ና ትንሹን ልጄን አሳድግ' እያለች ስታለቅስ እና የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት...." ባሏ በሠራዊቱ ውስጥ አገለጋይ ነው፣ ሁላችሁም ጁሊየስን ታውቃላችሁ፣ ብዙዎቻችሁ እዚህ —"አንድ ነቢይ አፍሪካን ጎበኘ" የሚለውን መጽሐፌን ጽፋችኋል።

እና ያቺ ምስኪን ድሃ ትንሽዬ ኖርዌጂያዊ እናት ድምጿን ከፍ አድርጋ እየጮኸች፣ “ወንድም ብራንሃም፣ ያ ሕፃን ከሞት ሲነሳ በዚያ ቆሜ ነበር፣ የክርስቶስ አገልጋይ እንደ ሆንህ እናምናለን” አለች። “ና እጅህን በልጄ ላይ ጫን፣ እናም ሕያው ይሆናል” አለች። አሁኑኑ በአንድ ወይም በሁለት አፍታ ውስጥ በሳንባ ምች ሞተ። ለአራት ወይም ለአምስት ሰዓት ያህል ታሞ ነበር።

እናም እነዚህ ሰዎች እየጮሁ እና እየዘለሉ፣ “እግዚአብሔር ከሞት ሊያስነሳዉ ነዉ! እግዚአብሔር ከሞት ሊያስነሳዉ ነዉ!!

እናም “በዚያ...” አሜሪካዊው... የአሜሪካ አየር መንገድ አይደለም፣ በዩናይትድ ስቴትስ የጦር ጀት በአንድ ቀን ውስጥ ሊመልሱኝ።

103 እኔም፣ “ከመምጣቴ በፊት የጌታን ፈቃድ ልወቅ” አልኩኝ። ስለዚህ ለሁለት ቀናት ጸለይኩ፣ እናም ያ ዶክተር በጣም ጥሩ ሰዉ ነዉ፣ ህጻኑ እዚያ እንዲተኛ አደረገዉ።

ከዚያም አንድ ቀን ማለዳ ተነስቼ ወደ ኩሽና መሄድ ጀመርኩ፣ እናም በዚያ ቆሜ ተመለከትኩኝ፣ በዚያ... የዚያን ብርሃን የሚያክል ሙብራት ፣ ዙሪያውን እየዞረ ፣ “ያንን አትንካ። ያንን አትቃወም። ያ የጌታ እጅ ነው” አለኝ።

ወዲያው ተመልሼ ሮጬ ሃላፊዉ ጋር ደወልኩና “መምጣት አልችልም” አልኩት።

እናም ይህ የሉተራን አገልጋይ፣ “እንደ ወንድም ብራንሃም ከእግዚአብሔር ግልጽ የሆነ ውሳኔ እስኪታገኝ ድረስ ለምን አትጠብቅም፣ ከዚያም የምትናገረውን ታዉቃለህ” አለው።

104 አሁን ያ ነው ወንድሞች። ዝም ብለን ድምዳሜ ላይ ባንደርስ እና ታግሰን ጠብቀን ግልጽ የሆነ ውሳኔ ከእግዚአብሔር ዘንድ ብናገኝ መልካም ነዉ። እናም ይህ ሁሉ እግዚአብሔርን የማያውቁ ኃጢአተኛ ፈዋሾች.... “መለኮታዊ ፈውስ የተመሰረተዉ በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ቀርባችሁ ልባችሁን ለእርሱ ስጡ እና ሕይወታችሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ታጠቡ በሚለው መርህ ላይ ነው” ብዬ አምናለሁ። ከዚያም እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ለመሥራት ይሄዳል አንተንም ይፈውስሃል። ልክ ይህ ወንድም በዚያ ስለ ጸለየላት ትንሽ ሴት - የእግዚአብሔር ቅዱሳን ፣ አያችሁ።

105 በህይወቴ ብዙ ስህተቶችን ሰርቻለሁ። ብዙ ስህተት የሆኑ ነገሮችን ሰርቻለሁ። ምናልባት ወደፊት ብዙ የምኖር ከሆነ ብዙ ስህተት እሰራለሁ። ምናልባት አንዳንዶቹ በሕይወታችሁ ላይ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ። ይቅር እንደምትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

የአብርሃምን ታሪክ እያነበብኩ ነበር- እንዴት ያጋጠመውን ብስጭት፣ እንዴት እርሱ ....የእኔ፣ ያደረጋቸውን ነገሮች! እግዚአብሔርን ተጠራጠረ፣ እናም ስለ ሚስቱ እና ስለ ሁሉም ነገር ዋሸ። ነገር ግን የእርሱ ሕይወት መለኮታዊ ሐተታ በሮሜ 4 ላይ በተጻፈበት ጊዜ፣ ስህተቶቹን ፈጽሞ አልተናገረም፣ ነገር ግን “አብርሃም እግዚአብሔር ላይ ባለዉ እምነቱ በፍፁም አላነከሰም... ባለማመን ጠንቅ አልወደቀም፣ ነገር ግን ጠንካራ ነበር” ብሏል። ስህተቶቹ ሁሉ የተረሱት የህይወቱ መለኮታዊ ማብራሪያ በተጻፈበት ጊዜ ነው። ብስጭቱ እንኳን አልተጠቀሰም። ስህተቶቹ አልተጠቀሱም። ወንድሞች፣ በዚያን ቀን የሕይወቴ ሃተታ በመለኮታዊ አይን ሲነበብ ልክ እንደ አብራሃም የኔንም ስህተት እንደሚያጠፋቸው ተስፋ አደርጋለሁ፣ ስለእነርሱም አያስብም። የእናንተም እንዲሁ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሄር ይባርካችሁ።

106 [ዶክተር ቶሚ ሂክስ የሚከተለውን አስተያየት ለመስጠት ወደ ማይክሮፎኑ ሄደ።

የተነገረውን ሁሉ ዛሬ ጠዋት በእነዚህ ቃላቶች ማጠቃለል የምንችል ይመስለኛል። የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእኔ ዉስጥ ነው። እባካችሁ እንደዚህ በሉ። የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእኔ ዉስጥ ነው።

በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ዉጣዉረዶች አሉ። (ተጨማሪ ንግግር አላደርግም) መልእክት አለኝ። እያንዳንዱ ክርስቲያን እንደ ነበረ አምናለሁ...?... ኢየሱስ...?... ዛሬ ጠዋት ልቤ ተነክቶቷል፣ እናም ለብዙዎቻችን አንዳንድ የሚረብሹን ነገሮች እንዳሉ አምናለሁ...?... የተሻልን የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ያደርጉናል።

ቤቤ ሩት የሆሜሩን ንጉስ በመባል ይታወቅ ነበር። ነገር ግን ቤቤ ሩት ተ ንጉስ እንደነበረ ታውቃላችሁ? የቤት ውስጥ ሩጫዎችን ካደረገው በላይ ብዙ ጊዜ በዉጭ አሸንፈ። እርሱ 1,330 ጊዜ አሸነፈ; 860 የቤት ሩጫዎችን ብቻ አድርጓል። ነገር ግን ቤቤ ሩት በተሸነፈ ቁጥር አሮጊቷ ዳኛ “ወጣህ” እያለ ሲጮህ ወደተቆፈረው ቦታ ተመልሶ እጁን እያሻሸ የሴሊት ወፍዋን አንስቶ አጥሩ ላይ ያመለክታል። እናም ሁል ጊዜም “በዚያ ፓይለር አዝኛለሁ” ይላል።

በመሸነፍ ምንም ስህተት የለም ነገር ግን አስታውሱ፡ የሌሊት ወፍ አንሳ...?... ምክንያቱም ክርስቶስ በእኔ ውስጥ የክብር ተስፋ ነው። እባክህ ደግመህ በለው፡ ክርስቶስ በእኔ ውስጥ የክብር ተስፋ ነዉ። ሁሉም ነገር ነው።]

አዎ።

[ሁሉም ነገር ነው።]

ትክክል ነው።

[ሁሉም ነገር ነው።]

ሁሉም ነገር። አሜን።

[ሃሌ ሉያ። በመጨቃጨቅ እና በመዋጋት መቼም ቢሆን ስራ አይሰራም።

በጣም ቅርብ ነን...]

አሜን።

[... ወደ ማዶ። ወደኋላ የማንመለስበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። የአውሮፕላን ካፒቴን “አሁን ወደኋላ መመለስ የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል”

ሲል ስንት ጊዜ ሰምቻለሁ።

ብዙም ሳይቆይ በቅርቡ “ልጄ ሆይ፣ ወደኋላ ማየትመለስበት ደረጃ ላይ ደርሰሃል” የሚል ድምፅ ከሌላ ዓለም ሰማሁ። እኔ ከጀመርኩበት ቦታ ይልቅ ወደ ሌላኛው ወገን እቀርባለሁ ማለት ነው።

አይናችሁን ጨፍኑ፣ እባካችሁ ጭንቅላታችሁን ዝቅ አድርጉ።

የሰማዩ አባታችን ሆይ፣ ዛሬ ጠዋት፣ ከልባችን እና ከጥልቅ ነፍሳችን፣ “ክርስቶስ በእኔ ዉስጥ—ክርስቶስ በእኔ ዉስጥ፣ የክብር ተስፋ” ለማለት በመቻላችን ምንኛ አመስጋኞች ነን። ኦህ፣ ኢየሱስ ሆይ፣ ወንድና ሴት ልጆችህን ሁሉ በፍቅር እጆችህ እቀፋቸዉ፣ እናም ራእያችን እና እይታችን ከዚህ አለም ነገሮች በላይ ከፍ፣ ከፍ፣ ከፍ ከፍ፣ ከፍ ከፍ ይበል። ክርስቶስን እንድናይ እና ሌሎችም ክርስቶስን በእኛ እንዲያዩ። በእነዚህ ባሪያዎችህ በእያንዳንዱ ላይ እጅህን ጫን…]

ጸጋን ስጠን፣ ጌታ ሆይ።

[… ዛሬ ጠዋት ከዚህ ቦታ ስንወጣ ከክርስቶስ በስተቀር ሌላ የሚያድን እንደሌለ አዉቀን እንድንወስን…]

ኣሜን።

[… እርስ በርሳቸው እንኳን ደህና መጣችሁ ተባባሉ። ሥራው ምን እንደሆነ እናውቃለን-መሰራት ያለበት ትልቅ ሥራ; ኢየሱስ; ታላቅ አጨዳ ያለበት።]

አዎ ጌታ ሆይ።

(ጌታ ሆይ እርዳን…)

አዎ ጌታ ሆይ።

[…እጃችንን አንድ ላይ እንድንያያዝ…]

ፀጋዉን አብዛልን ጌታ ሆይ።“

[እናም መከሩን እንድንሰበስብ…]

አዎን ጌታ ሆይ።

[…የጠፉትን እና ሊሞቱ ያሉትን ጊዜው ከማለፉ በፊት ለመመለስ።]

አዎን ጌታ ሆይ።

[እጆቻችሁን አንሥታችሁ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እንድታወድሱ እፈልጋለሁ።]

[ወንድም ብራንሃም እና ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።]

[እባካችሁ እንቁም። ከእኔ ጋር እጆቻችሁን አንስታችሁ እንድትዘምር እፈልጋለሁ። “እኔ እወደዋለሁ” እናንተ ትወዱታላችሁ…]

ኣሜን።

[… ዛሬ ጠዋት? በሙሉ ልባችሁ ትወዱታላችሁ? እጆቻችሁን አንሡ እና ዘምሩት፣ ሁላችሁም በአንድነት፣ “እወደዋለሁ”።

እወደዋለሁ፣ እወደዋለሁ፣

ምክንያቱም እሱ መጀመሪያ ስለወደደኝ

መዳኔን ፈጸመ

በቀራንዮ ዛፍ ላይ.

እባካችሁ ከልባችሁ አንጎራጉሩ።

ታውቃላችሁ፣ አብራችሁን የምታገለግሉ አገልጋዮች፣ በአርጀንቲና በአንድ አገልግሎት ከ400,000 በላይ ሰዎች ነበሩ። ህዝቡን ከጊዜ ወደ ጊዜ አይተናል። እናም በመጀመሪያው ከሰአት በኋላ ከ400,000 የሚበልጡ ሰዎች በስፓኒሽ ይዘፍኑ ነበር እናም በልባቸዉ እንዲያዜሙ አድርጌአቸዋለሁ፣ እናም ውጪ ከ300,000 በላይ ሰዎች ነበሩ። በውስጥ ያሉትን ሰዎች ዝም እንዲሉ አድርገን በዉጭ ያሉት ደግሞ የዚያን መዝሙር ቃላት እንዲያዜሙ ጠየቅናቸው። እናም በድንገት፣ እያዜሙ፣ አንድ የሆነ ነገር ነፍሴን አጥለቀለቃት። በዚያ ውጭ ያሉት የ300,000 ሰዎች የሚያስተጋባ “እወደዋለሁ” የሚል ዜማ እስከሰማሁባት ሰዓት ድረስ በህይወቴ ክርስቶስ በእኔ ዉስጥ የሚለዉን ቃል መገለጥ አላውቅም ነበር። ዛሬ ጠዋት ታላቅ ግርማ ሞገስ ያለው የክብር ንጉስ ሰራዊት ነው፣ እናም ይዘምራሉ። ማንን ይወዳሉ? ማንን ነው ትወዳላችሁ?]

አዎን።

[ክርስቶስ፣ ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ነዉ።]

*አዎን።*

[የክብር ተስፋ። አይናችሁን ጨፍኑ፣ እጆቻችሁን አንሡ እናም እንደገና ዘምሩ፣ ሁላችሁም።]

*አዎን ጌታ ሆይ።*

[እወደዋለሁ፣ እወደዋለሁ፣

*መጀመሪያ* ስለወደደኝ

*መዳኔን ፈጸመ*

በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

ዛሬ ጠዋት እርሱን ከወደዳችሁት፣ እጆቻችሁን በሶስት ወይም በአራት የተለያዩ ሰዎች ዙርያ አድርጉ፣ እናም ሴቶችም እንዲሁ አድርጉ፣ እና “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እወደዋለሁ” በሉ። ልክ ነው። እጆቻችሁን አዙሩ...]

107 [ይህንን የፍቅር ምላሽ ተከትሎ፣ ወንድም ብራንሃም ወደ ማይክሮፎኑ ተመለሰ—ኤድ።] ይህ በመላው አለም ሲከሰት ማየት ከቻልኩ፣ “ጌታ ሆይ፣ ባሪያህን በሰላም አሰናብተዉ” እላለሁ።

ስብከት በ

**ዊልያም ማርዮን ብራንሀም**

"... ድምጹም በሚሰማበት ዘመን ..." ራእይ 10፡7

www.messagehub.info